# ምዕራፍ 6

## ምእመናንን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ማዘጋጀትና ማሰለፍ

የቤተ ክስቲያን ተልእኮ ክፍል የሆነው ሌላው መሠረታዊ ነገሮች ምእመናንን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ማዘጋጀትና ማሰለፍ ነው ። እግዚአብሔር ሰውን የሚጠራው ለሁለት ነገር ነው ።

1ኛ/ ለዘላለም ሕይወት ፥ 2ኛ/ለመንፈሳዊ አገልግሎት ነው ። አምልኮ ግን የሁለቱም እንብርት ነው ።

ምእመናን እነዚህን መሠረታዊ ነገሮች እንዲያውቁና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንዲኖሩ ቤተ ክርስቲያን ማስተማር አለባት።

የተሰሎንቄ ሰዎች ከሰይጣን ግዛት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንደተመለሱና ለእግዚአብሔር መንግስት እንደተሰለፉ በአንደኛ ተሰሎንቄ 1:9 ተጽፎ እናገኛለን ። ይህን አሳብ ሲገልጥ ፥ ሐዋርያ ጳውሎስ እንዲህ ይላል ፥ “ .....ሕያውና እውነተኛ



የሆነውን አምላክ ለማገልገል ከጣኦቶችም ወደ እግዚአብሔር እንዴት እንደ ተመለሳችሁ እነርሱ ራሳቸው ይመሰክራሉ ። ”

በአንደኛ መልእክቱ 2:9 ሐዋርያ ጴጥሮስ ስለ ምእመናን አገልግሎት አስፈላጊነት እንዲህ ይላል ፥ “ እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእግዚአብሔርን አስደናቂ ሥራ እንድታውጁ የተመረጠ ትውልድ ፥ የንጉሥ ካህናት ፥ እግዚአብሔር ለራሱ ያደረጋችሁ ቅዱስ ሕዝብ ናችሁ ። ”

በዚህ ጥቅስ እንደተመለከትነው ፥ 1ኛ/ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር የሚጠሩት ለዘላለም ሕይወት መሆኑን ያሳያል ። 2ኛ/ ምእመናን በሙሉ ( እያንዳንዱ አማኝ ) እግዚአብሔርን እንዲያገለግል መጠራቱን ያመለክታል ። 3ኛ/እያንዳንዱ አማኝ ይህን ተገንዝቦ እግዚአብሔር በሰጠው የአገልግሎት መክሊት እንዲሰለፍ ሐዋርያ ጴጥሮስ ሲያስተምር እናያለን ። ዛሬም ምእመናን ይህን እንዲገነዘቡና ለመንፈሳዊ አገልግሎት እንዲሰለፉ ማስተማር የቤተ ክርስቲያን ተግባር ነው ።

ይህን አስመልክቶ ሐዋርያ ጳውሎስ በኤፌ 4:11-13 ግሩም የሆነ መሠረታዊ ትምህርትን ለቤተ ክርስቲያን አስተላልፎአል ። ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ፥ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን እንደሰጠ በኤፌ 4:11 ተጠቅሶአል ። በኤፌ 4:12-13 ባለው ክፍል እነዚህን አገልጋዮች የሰጠበትን ምክንያት ይገልጣል ።

አንዱ ምክንያት :- ከዚህ ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ፥ የምእመናንን መንፈሳዊ ሕይወት ለማነጽ ነው ። ሁለተኛው ምክንያት ምእመናንን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ማዘጋጀትና ማሰለፍ

ነው ። ለምሳሌ ፦"እነርሱም አንዳንዶች ሐዋርያት ፣ አንዳንዶቹ ነቢያት ፣ አንዳንዶቹ የወንጌል ሰባኪዎች ፣ አንዳንዶቹ የምእመናን እረኞች ፣ አንዳንዶቹ አስተማሪዎች እንዲሆኑ ስጦታዎችን ሰጠ ። ይህንንም ያደረገው የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽ ምእመናንን ለክርስትያናዊ አገልግሎት ለማዘጋጀት ነው "ይላል ( ኤፌ 4:11-12 ) ።

በእነዚህ ጥቅሶች እንደተገለጠው ፣ ቤተ ክርስቲያን ወደ ጌታ የተመለሱትን ሰዎች ወይም ምእመናን መንፈሳዊ ሕይወታቸዉን ማነጽ ብቻ ሳይሆን ፣ ምእመናንን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ማዘጋጀትና ማሰለፍ እንዳለባት በግልጥ እናያለን ።

ሐዋርያ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ለመንፈሳዊ አገልግሎት እንዳዘጋጀዉና ለአገልግሎት እንዳሰለፈው በ 2ኛ ጢሞ 2:1-2 ገልጦለታል ። ከዚህም በላይ ጢሞቴዎስና እርሱ የሚያገለግላት ቤተ ክርስቲያን በዚሁ መሠረት ሌሎች ምእመናንን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ማዘጋጀትና ማሰለፍ እንዳለባቸው ጢሞቴዎስን በጥብቅ ያሳስበዋል ። ለምሳሌ ፦" በብዙ ምስክሮች ፊት ከእኔ የተማርከዉን ትምህርት ሌሎችን ለማስተማር ችሎታ ላላቸውና ለታመኑ ሰዎች አስተላልፍ " ይላል ( 2ኛ ጢሞ 2:2 ) ።

ከነፍስ ደህንነት አንጻር ስንመለከት ምእመናን ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እኩል ናቸው ። ይህም ማለት ፦የሐዋርያ ጳውሎስ ደህንነት ከእኔ ደህንነት በምንም አይነት አይበልጥም ። እርሱን ለማዳን ክርስቶስ መሞት እንደነበረበት ሁሉ እኔንም ለማዳን ክርስቶስ መሞት ነበረበት ። ጳውሎስ በእምነት ብቻ እንደዳነ ሁሉ እኔም በእምነት ብቻ ድኛለሁ ። እርሱ የዘላለም ሕይወት እንዳለው ሁሉ እኔም የዘላለም ሕይወት አለኝ ።



ሐዋርያ ጳውሎስ ራሱ ይህን ትምህርት ሲያስተምር እንዲህ በማለት ጽፎአል ፤ " ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ባላችሁ ሕብረት በእምነት አማካይነት ሁላችሁም የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ ። ምክንያቱም በጥምቀት ከክርስቶስ ጋር አንድ የሆናችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋል ። ሁላችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ስለሆናችሁ በአይሁዳዊና በግሪካዊ ፣ በአገልጋይና በጌታ ፣ በወንድና በሴት መካከል ምንም ልዩነት የለም ። እንግዲህ የክርስቶስ ከሆናችሁ ፣ የአብርሃም ዘር ናችሁ ፣ በተስፋውም ቃል መሠረት ወራሾች ናችሁ ። " ( ገላ 3:26-29 ) ።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች ግልጥ ባለ ሁኔታ ፣ ምእመናን ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናቸዉንና አንዱ አማኝ ከሌላው አማኝ እንደማይበልጥ ያሳያሉ ።

ይሁን እንጂ የአገልግሎት ሃላፊነት አንድ አይደለም ። እግዚአብሔር ምእመናንን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ሲያሰልፍ የተለያዩ ሐላፊነቶችን ይሰጣቸዋል ። ከዚህ ቀጥሎ ያለዉን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ልብ ብለን ብንመለከት ይህን ለመረዳት እንችላለን ።

" በአንዱ አካላችን ብዙ ክፍሎች አሉ ፣ እያንዳንዱም የአካል ክፍል የተለየ ሥራ አለው ። እንዲሁም እኛ ብዙዎች ሆነን ሳለን በክርስቶስ አንድ አካል ነን ። የአንዱ አካል ክፍሎች እንደመሆናችንም መጠን እርስ በእርሳችን ተገጣጥመናል ። ስለዚህ እግዚአብሔር በጸጋው የሰጠንን ልዩ ልዩ ስጦታ በሥራ ላይ እናውል ፤ ሥጦታችን የትንቢት ቃል መናገር ከሆነ ፣ በእምነታችን መጠን የእግዚአብሔርን ቃል እንናገር ። ሥጦታችን ሌሎችን

ማገልገል ከሆነ ፥ በትጋት እናገልግል ፤ ስጦታችን ማስተማር ከሆነ ፥ በሚገባ እናስተምር ፤ ስጦታችን መምከር ከሆነ ፥ እንምከር ፤ ስጦታችን ማስተዳደር ከሆነ ፥ በትጋት እናስተዳድር ፥ ስጦታችን ምህረት ማድረግ ከሆነ ፥ በደስታ ምህረት እናድርግ ” ( ሮሜ 12:4-8 ) ።

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የሐዋርያ ጳውሎስ ትምህርት እንደሚያሳየን ክርስቲያኖች የአንድ አካል ክፍሎች ነን ። አብረን ለዘላለም ህይወትና ለአገልግሎት የተጠራን ነን ። ነገር ግን ምንም እንኳ የአንድ አካል ክፍሎች ብንሆንም ፥ “ እያንዳንዱ የአካል ክፍል የተለየ ” አገልግሎት አለው ። “ ስለዚህ እግዚአብሔር በጸጋው የሰጠንን ልዩ ልዩ ስጦታ በሥራ ላይ እናውል ” ሲል ጳውሎስ ያስተምረናል ( ሮሜ 12:6) ።

ስለዚህ ሁሉም እንደየስጦታውና እንደየጥሪው በመንፈሳዊ አገልግሎት እንዲሰለፍ የጌታችን ፈቃድና ጥሪ ነው ። አማኝ ሁሉ የጸጋ ስጦታ አለው ። ስጦታዎቹ የተለያዩ ናቸው ። ስለሆነም በተሰጠን ስጦታና በተጠራንበት መስመር መሰለፍ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት የተሟላ ያደርገዋል ።

ሐዋርያ ጳውሎስ ይህን እውነት ሲያስገነዝበን እንዲህ ይላል ፥ “ ነገር ግን ሁሉም ሐዋርያት አይደሉም ፤ ሁሉም መምህራን አይደሉም ፤ ሁሉም ተአምራትን የሚያደርጉ አይደሉም ፤ ሁሉም የመፈወስ ስጦታ የላቸውም ፤ ሁሉም በአዲስ ቋንቋ የመናገር ስጦታ የላቸውም ፤ ሁሉም በአዲስ ቋንቋ የተነገረውን የመተርጎም ችሎታ የላቸውም ” ( 1ቆሮ 12:29-31 ) ።

ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን ለመንፈሳዊ አገልግሎት



እያሰለጠነች /እያዘጋጀች ካላሰለፈች ብዙ ችግሮች ይፈጠራሉ ። ሊፈጠሩ ከሚችሉት ችግሮች መካከል አንዳንዶቹን ከዚህ ቀጥዬ ልጥቀሳቸው።

1ኛ/ምእመናን ለአገልግሎት ካልተሰለፉ የወንጌል አገልግሎት በሚገባ ሁኔታ ሊስፋፋ አይችልም ። የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ አንዱ ክፍል ሰዎችን ወደ ጌታ መመለስ ነው ብለናል ። ነገር ግን ምእመናን ለዚህ አገልግሎት ታጥቀው ካልተሰለፉ ይህ ተልእኮ አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ ሊከናወን አይችልም ።

2ኛ/ ቤተ ክርስቲያን ከምእመናን መካከል እግዚአብሔር ለአገልግሎት የቀባቸዉን ለዚህ ለተጠሩበት አገልግሎት ካላዘጋጀችና ካላሰለፈች ፥ ወደ ቤተ ክርስቲያን እየመጡ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚቀበሉትን አዳዲስ አማኞች የጉባኤው አካል ሆነው በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዲቀሩ ለማድረግ አትችልም ።

እነዚህን አዳዲስ አማኞች ወዲያዉኑ ወስደው የደህንነትን ትምህርት በማስተማር የጀመሩትን መንፈሳዊ ጉዞ እንዴት መጓዝ እንዳለባቸውና ሕይወታቸውን እንዴት መምራት እንዳለባቸው ካልረዱዋቸውና የጉባኤው /የቤተ ክርስቲያን አባል እንዲሆኑ ካላደረጉአቸው በስተቀር የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አንካሳ አገልግሎት ይሆናል ።

በየሳምንቱ ጌታን ለመቀበል እጆቻቸዉን የሚያሳዩ ሰዎች ቁጥርና ቋሚ አማኞች ሆነው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጸንተው የሚቀሩ ሰዎች ቁጥር ተመጣጣኝ አይሆንም ። ይህ ሲሆን “ ሰዎች በፊት ለፊት በር ገብተው በጓሮ በር ይወጣሉ ” እንደሚባለው ፥ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በየሳምንቱ እጆችን መቁጠር

ብቻ ሆኖ ይቀራል ።

3ኛ/ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን ለመንፈሳዊ አገልግሎት አዘጋጅታ ካላሰለፈች ፥ የምእመናን መንፈሳዊ ሕይወት ሊታነጽ አይችልም ። ምእመናን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ካልታነጹ ሁል ጊዜ ሕፃናት ሆነው ይቀራሉ ። መንፈሳዊ ሕይወታቸው ጥልቀት የሌለው ፥ በስህተት ትምህርት በቀላሉ የሚወሰዱ ፥ በችግር ጊዜ በቶሎ የሚወድቁና በቤታቸውም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኃላፊነት መዉሰድ የማይችሉ ይሆናሉ ።

4ኛ/ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን ለመንፈሳዊ አገልግሎት አዘጋጅታ ካላሰለፈች በአገልግሎት ላይ ያሉት አገልጋዮች ትልቅ ውጥረት ውስጥ ይገባሉ ። ምክንያቱም አገልጋዮቹ ጥቂት ሲሆኑ አገልግሎቱግን ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ መስጠት ያለባቸዉን አገልግሎቶች ሁሉ ለመስጠት አይችሉም ።

በአገልግሎት ላይ ያሉት አጋልጋዮች ጊዜም እንኳ ቢኖራቸው ፥ ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎች የሚያስፈልጉዋቸዉን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች በተሟላ ሁኔታ ለመስጠት አይችሉም ። ምክንያቱም አንድ አገልጋይ ሁሉንም የጸጋ ስጦታዎች ሊኖሩት አይችሉም ። ስጦታዎቹ የተወሰኑ እንደመሆናቸው መጠን የአገልግሎቱም መድረኮች የተወሰኑ ይሆናሉ ።

ከዚህ የተነሳ አገልጋዮች ውጥረት ውስጥ ይገባሉ ። የሕሊና ወቀሳም ያስቸግራቸዋል ። የሰይጣን ክስ አእምሮአቸውን ይደበድባል ። አገልግሎት በደስታ መንፈስ የሚሰጥ መሆኑ ቀርቶ ሸክምና የግዴታ ጉዳይ እየሆነ ይሄዳል ።



በዚህ ዓይነት ውጥረት የሚሰጠው አገልግሎት በአገልጋዮች መንፈሳዊ ሕይወት ላይ ፥ በቤተሰባቸው ሕይወት ላይና በትዳራቸው ላይ አሳዛኝ ቀዉስን ያመጣል ። በተጨማሪም ይህ የዉጥረት አገልግሎት አገልጋዮች በቂ ጊዜ አግኝተው የእግዚአብሔርን ቃል በጥሞና በማጥናትና በጸሎት በመትጋት ሕይወታቸዉንና አገልግሎታቸውን እንዳያዳብሩ ያደርጋቸዋል ።

5ኛ/እግዚአብሔር ለልዩ ልዩ አገልግሎት የቀባቸው ምእመናን ስልጠና ተሰጥቶዋቸው እንደ ስጦታቸው መጠን ለአገልግሎት ካልተሰለፉ በእነዚህ ጥሪ ባላቸው ምእመናን ሕይወት ውስጥ ደስ የማያሰኙ ነገሮች ሊፈጠሩ ይችላሉ ። ሊፈጠሩ ከሚችሉት ነገሮች ጥቂቶቹን ልጥቀስ ።

አንደኛ :- በአገልግሎት ላይ ባሉት አገልጋዮች ላይ ጥላቻ እንዲያድርባቸው ሊያደርግ ይችላል ። ሁለተኛ :-መነጫነጭንና ማጉረምረምን በሕይወታቸው ሊያመጣ ይችላል ። ሦስተኛ :- የማመጽንና የእንቢተኝነትን መንፈስ በሕይወታቸው ሊፈጥር ይችላል ። አራተኛ :-የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት በሚጎዳ ፥ ሕብረትን በሚከፋፍል ፥ ሕይወታቸውን በሚያቃውስ ፥ የወደፊቱን የአገልግሎት እድላቸውን በሚያበላሽና በውጭም ነቀፋን በእግዚአብሔር ስምና ሕዝብ ላይ በሚያስከትል ሁኔታ በራሳቸው አገልግሎት እንዲጀምሩ ሊገፋፋቸው ይችላል ።

ከሁሉም በላይ ፥ ነፍሳት እንዲድኑበት ፥ ምእመናን እንዲታነጹ በትና ሌሎች አገልጋዮችም የአገልግሎት ጸጋቸውን በበለጠ እንዲያሳድጉበት እግዚአብሔር ለቤቱ የሰጠው ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎች አገልግሎት ላይ ሳይዉሉ እንዲያው በከንቱ ተቀብረው ይቀራሉ ። ይህ እግዚአብሔርን አያስደስተዉም ።

እዚህ ላይ በጣም የጠበቀ ማሳሰቢያ ለመስጠት እፈልጋለሁ ። "ቤተ ክርስቲያን በአገልግሎት አላሰለፈችኝም " በማለት ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ጎጂና ክርስቲያናዊ ባልሆኑ ነገሮች ውስጥ ራስን ማስገባት እጅግ በጣም አደገኛ ይሆናል ። ስለዚህ እያንዳንዱ አማኝ ከነዚህ ነገሮች ራሱን መጠበቅ አለበት ።

አመጸኝነት ፥ እንቢተኝነት ፥ ምሬት ፥ ሕብረትን መከፋፈል ፥ የእግዚአብሔርን ስምና ሕዝብ በውጭ ሰዎች ማሰደብ ፥ የቅዱሳንን መንፈስ ማሳዘን ከእግዚአብሔር መንፈስ አይደለም ። የራስን ሕይወት በእነዚህ ነገሮች ማስመረዝ ወደ ጥፋት ያደርሳል ። ራስንም ለሰይጣን ማጋለጥ ይሆናል ። ስለዚህ መጠንቀቅ ነው!

እንግዲህ ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው ከቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ዋና ዋናዎቹ ክፍሎች አንዱ ምእመናን የጸጋ ስጦታቸዉን እንዲለዩና እንዲያዳብሩ ማዘጋጀት ነው ። ከዚሁ ጋር የተያያዘው ነገር ደግሞ ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ምእመናን ለአገልግሎት ካዘጋጀች በኋላ እያንዳንዱን አማኝ እንደ ስጦታውና እንደ ፈጣሪው ፈቃድ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ማሳለፍ ነው ።



# ምዕራፍ 7

## እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ ማምለክ

ቀደም ብዬ ባሳየሁት ስዕላዊ መግለጫ መሠረት ሰዎችን ወደ እግዚእብሔር የመመለስ ፥ የምእመናንን መንፈሳዊ ሕይወት የማነጽ ፥ ምእመናንን ለመንፈሳዊ አገልግሎት የማዘጋጀትና የማሳለፍ እንብርት የሆነው ሕያው እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ ማምለክ ነው ።

1ኛ/ ሰዎችን ወደ እግዚእብሔር መመለስ እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ በማምለክ ላይ ካልተመሠረተ መልካም ውጤት ያለውና እግዚአብሔርን የሚያስከብር አገልግሎት ነው አያሰኝም።

2ኛ/ የምእመናንን መንፈሳዊ ሕይወት ማነጽ ፥ እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ በማምለክ ላይ ካልተመሰረተ ብዙ በረከት የለዉም ።

3ኛ/እንዲሁም ምእመናንን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ማሰለፍ እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ በማምለክ ላይ ካልተመሠረተ አገልግሎት መንፈሳዊ አገልግሎት ነው ለማለት ያስቸግራል ።

እግዚአብሔርን በግለሰብ ደረጃና በቤተ ክርስቲያን ወይም በጉባኤ ደረጃ እናመልካለን ።

በእብራውያን ቋንቋ ፥ " እግዚአብሔርን ማምለክ " የሚለው ቃል " እግዚአብሔርን ማገልገል " የሚለዉን ትርጉም ይሰጣል ። ስለዚህ በአንድ ቦታ " እግዚአብሔርን ማምለክ የሚለዉን ቃል በሌላ ቦታ " እግዚአብሔርን ማገልገል " ብለው ይተረጉሙታል።

ለምሳሌ :- በዘጸ 4:23 " ልጄ ( እሥራኤል ) እኔን ማምለክ ይችል ዘንድ እንድትለቀው ነገርሁህ " ተብሎ የተነገረዉን ቃል በዘጸ 8:1 ደግሞ "ያገለግለኝ ዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ " ይለዋል።

ሰፋ ባለ አነጋገር :- በመልካም ሕሊናና በንጹህ ልብ ለእግዚአብሔር የቀረበው አገልግሎት እንደ አምልኮት ይቆጠራል ስለዚህ "ያመልከኝ ዘንድ " ተብሎ ቢተረጎምም አሳቡ ያው ስለሆነ ሁለቱም አተረጓጎም ልክ ናቸው ።

ሕያው እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ ማምለክ በሚለው ርእስ ሥር :- " ማምለክ " የሚለዉን ቃል ጠበብ አድርገን የወሰድነው እንደሆነ " እግዚአብሔርን ማምለክ " የሚለው ቃል የሚከተሉትን አራት ፍሬ ነገሮች ያካትታል ።

1ኛ/የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ ወይም መስማት
2ኛ/ እግዚአብሔርን ማወደስ



3ኛ/ እግዚአብሔርን ማመስገን
4ኛ/ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ

ከዚህ ቀጥሎ እነዚህን አራት ፍሬ ነገሮች በመጠኑ ዘርዝረን እንመልከት ።

## 1ኛ/የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ ወይም መስማት

ከአራቱ የአምልኮ ክፍሎች አንዱ የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ ወይም መስማት ነው ። በግለሰብ ደረጃና በቤተሰብ ደረጃ በሚደረገው አምልኮ ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል ይነበባል ። በቤተ ክርስቲያን ወይም በጉባኤ በሚደረገው የአምልኮ ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል በንባብም መልክ ሊቀርብ ይችላል ።

በግለሰብ ደረጃና በቤተሰብ ደረጃ በሚደረገው አምልኮ የቃሉ ንባብ ቢቀድም መልካም ይሆናል ። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል አስቀድሞ ሲነበብ ያ ቃል እግዚአብሔርን ወደ ማወደስ ፥ ወደ ማመስገንና ወደ ጸሎት የሰዉን መንፈስ ይመራል ።

ቃሉ የእግዚአብሔርን ማንነትና የሰውን ማንነት ሲያሳየን እግዚአብሔርን እንደሚገባን ለማምለክ ይረዳናል ። ሰው በእውነትና በመንፈስ ሕያው እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚችለው የእግዚአብሔርን ማንነትና የሰውን ማንነት በሚገባ ሲረዳ ነው ።

የእግዚአብሔር ቃል መንፈሳዊ አይናችንን ሲከፍት ፥ ውስጣዊ ልባችንን ሲመረምር ፥ ልባችንን በመለኮታዊ እሳት

ሲያቀጣጥልና የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ባሕርይ ሲያሳየን በእውነትና በመንፈስ ማምለክ እንጀምራለን ።

ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ ከአራቱ የአምልኮ ክፍሎች አንዱ ነው ።

2ኛ/ እግዚአብሔርን ማወደስ :-

እግዚአብሔርን ማወደስ የአምልኮ ክፍል ነው ። ማወደስ ማለት :- ከፍ ከፍ ማድረግ ፥ ማሞገስ ፥ እጅግ በጣም ማክበር ማለት ነው ። ማወደስ ጸሎት ወይም ልመና አይደለም ። ማወደስ ራሱን የቻለ የአምልኮ ክፍል ነው ። እግዚአብሔርን የምናወድሰው ስለ ማንነቱ ነው ።

እግዚአብሔርን ስናወድሰው የመለኮት ባሕርይውን እያሰብን ነው ። ለምሳሌ :-በእግዚአብሔር ፊት ለአምልኮ ስንቀርብ ፈጣሪነቱን ፥ ታላቅነቱን ፥ ገዢነቱን ፥ ፈራጅነቱን ፥ አዳኝነቱን ፥ ጻድቅነቱን ፥ ሁሉን ቻይ መሆኑን ፥ ሁሉን አዋቂ መሆኑን ፥ በሁሉ ቦታ መገኘቱንና እነዚህን የመሳሰሉትን አስደናቂ የሆኑትን ባሕርያት እናስባለን ።

በዚሁ አንጻር ደግሞ የራሳችንን ኢምንትነት እንገነዘባለን ። በመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ጥቅሶች ብንመለከት የበለጠ አሳቡን ግልጥ ያደርጉልናል ።

" ኑ በእግሩ ሥር ወድቀን እንስገድለት ፥ ፈጣሪያችን በሆነው በእግዚአብሔር ፊት እንንበርከክ ። እርሱ አምላካችን ነው ፤ ......እኛም መንጋዎቹ ነን " ( መዝ 95:6 ) ።



" ....ሁሉን የምትችል እግዚአብሔር ሆይ አንተ የምድር ሁሉ ገዥ ነህ ፤ ከአማልክት ሁሉ ይልቅ ከፍ ያልህ ነህ " ( መዝ 97:9 ) ።

" ....ሁሉን የምትችል ጌታ አምላክ ሆይ ! ሥራህ ታላቅና አስደናቂ ነው ፤ የሕዝቦችህ ንጉሥ ሆይ መንገድህ ትክክልና እውነት ነው ፥ ጌታ ሆይ ! አንተን የማይፈራና ስምህን የማያከብር ማን ነው ?ምክንያቱም ቅዱስ አንተ ብቻ ነህ ፤ የእውነት ፍርድህ ስለተገለጠ ፥ ሕዝቦችህ ሁሉ መጥተው በፊትህ ይሰግዳሉ " ( ራዕ 15:3-4 ) ።

" ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች ዘላለም በሚኖረው ፥ በዙፋኑ ላይ በተቀመጠው ፊት በግንባራቸው ተደፍተው ይሰግዳሉ ፥ አክሊሎቻቸውንም በዙፋኑ ፊት አኑረው ' ጌታችንና አምላካችን ሆይ ! ሁሉን ነገር ስለፈጠርህ ፤ ሁሉም ነገር የተፈጠረውና መሆንን ያገኘው በአንተ ፈቃድ ስለሆነ ክብርና ውዳሴ ኃይልም መቀበል የተገባህ ነህ ' ይሉ ነበር " ( ራዕ 4:10-11 ) ።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች እግዚአብሔርን ስለ ማንነቱ ብቻ ማወደስ እንዴት እንደሆነ ያሳያሉ ። ሰው በፈጣሪው ፊት ይህንን በመሰለ ሁኔታ ቀርቦ አምላኩን ከፍ ከፍ ሲያደርግ አምልኮ ማድረጉ ነው ። ስለዚህ ለእግዚአብሔር የሚቀርበው ውዳሴ የአምልኮ ክፍል ነው ።

### 3ኛ/ እግዚአብሔርን ማመስገን

እግዚአብሔርን ማመስገን ከአራቱ የአምልኮ ክፍሎች አንዱ ነው ። እግዚአብሔርን የምናወድሰው ስለ ማንነቱ ነው ብለናል ። እግዚአብሔርን የምናመሰግነው ስለ ማንነቱ ሳይሆን ስላደረገልን መልካም ነገሮች ነው ። የምስጋናና የውዳሴ ልዩነት ይህ ነው።

ምስጋና ለእግዚአብሔር የምናቀርበው እርሱ ስላደረገልን መልካም ነገሮች መሆኑን የሚያሳዩንን ጥቅሶች ለምሳሌ ያህል ከዚህ ቀጥሎ እንመልከት ።

" አምላኬ ሆይ ! ስላዳንከኝና ጠላቶቼ በእኔ ላይ እንዲደሰቱ ስላላደረግህ አመሰግንሃለሁ " ( መዝ 30:1 ) ።

" አንተ ሃዘኔን ወደ ደስታ ለወጥህልኝ ፤
ትካዜዬን ከእኔ አስወገድክልኝ ፤
በደስታም ሞላኸኝ ።
ስለዚህ ዝም አልልም ፤
ለአንተ የምስጋና መዝሙር አቀርባለሁ ።
እግዚአብሔር ሆይ ! አንተ አምላኬ ነህ ፤
ስለዚህ ለዘላለም አመሰግንሃለሁ "
( መዝ 30:11-12 ) ።

"ነገር ግን እኛን ዘወትር በክርስቶስ ድል አድራጊዎች አድርጎ ለሚመራን መልካም መአዛ እንዳለው ሽቶ ስለ ክርስቶስ ያለንን እውቀት በየስፍራው ሁሉ እንድናደርስ ለሚያደርገን አምላክ ምስጋና ይሁን " ( 2ቆሮ 2:14 ) ።

" እንግዲህ እኛ የማትናወጠውን መንግሥት ስለምንወርስ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን " ( ዕብ 12:28 ) ።



ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች ፣ ምስጋና ለእግዚአብሔር የምናቀርበው እርሱ ስላደረገልን መልካም ነገሮች መሆኑን ያመለክታሉ ። ምስጋናም ውዳሴም በዝማሬም መልክ ሊቀርቡ ይችላሉ ። ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው ምስጋና ከአምልኮ ክፍል አንዱ ነው ።

## 4ኛ/ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ

ጸሎትን በአምልኮት ክፍል መመደብ ትክክል መስሎ የማይታያቸው ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ ። የእግዚአብሔርን ማንነትና የሰዉን ማንነት በሚገባ ብንገነዘብ ጸሎት የአምልኮት ክፍል መሆኑን ለማየት አያስቸግርም ።

ምክንያቱም ሰው ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ባህሪያት ያሳያል ። ይህም ማለት እግዚአብሔር የፍጥረት ሁሉ ፈጣሪ ፣ የኃያላን ሁሉ ኃያል ፣ የገዥዎች ሁሉ ገዥ ፣ ሁሉን አዋቂ ፣ ሁሉን ነገር ማደረግ የሚችል ( ከኃጢአት በቀር ) ፣ በአንድ ጊዜ በሁሉም ቦታዎች የሚገኝ ፣ ሰው ማስወገድ ወይም ማስገኘት የማይቻለዉን ለማስወገድ ወይም ለማስገኘት የሚችል መሆኑን ያሳያል ።

በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት በትህትና በመቅረብ ፣ በንስሐ ፣ በምልጃና በጸሎት የእግዚአብሔርን ፍቅር ፣ ምህረት ፣ ይቅርታ ፣ ቸርነትና ርህራሄ ይጠይቃል ። እነዚህን ሁሉ ሲጠይቅ በሰው ልጅ ማንነት ላይ በመመስረት ሳይሆን በእግዚአብሔር ማንነት ላይ በመመስረት ነው ።

ስለዚህ ጸሎት የአምልኮ ክፍል ነው ። ጸሎት ልመና ነው ። ጸሎት መጠየቅ ነው ። የአምልኮት ጸሎት በሶስት ክፍል ይከፈላል ።

## ሀ/ ስለራስ ኃጢአት ይቅርታን መጠየቅ

እውነተኛ ጸሎት በንስሐ ይጀምራል ። ነቢዩ ኢሳያስ በቅድስና ፥ በግርማ የተሞላውን ልዑል እግዚአብሔርን በታላቁ ዙፋን ላይ ተቀምጦ መላእክት በታላቅ አክብሮት ሲያገለግሉት ባየ ጊዜ የራሱንም ኃጢአተኛነት ተገነዘበ ። ይህ ግንዛቤ ወደ ንስሐ መራው ።

“ እኔም እነሆ ከንፈሮቼ በረከሱበት ሕዝብ መካከል የምኖር ፥ ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው ነኝ ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርን በዐይኖቼ አይቻለሁና መጥፋቴ ስለሆነ ወዮልኝ አልሁ ” ( ኢሳ 6:5 ) ።

ንጉሡ ዳዊት ኃጢአተኛነቱን በተገነዘበ ጊዜ የኃጢአት ይቅርታ ለማግኘት እንዲህ ሲል ወደ እግዚአብሔር ጸለየ ።

“ አምላክ ሆይ ! ስለ ዘላለማዊ ፍቅርህ ይቅር በለኝ ፤ ስለ ታላቁም ምህረትም ኃጢአቴን ደምስስልኝ ። በደሌን ሁሉ አጥበህ አስወግድልኝ ፤ ከኃጢአቴም አንጻኝ ። እኔ ስህተቴን አውቃለሁ የኃጢአቴንም ብዛት ዘወትር እገነዘባለሁ ” ( መዝ 51:1-3 ) ።



## ለ/ ለራስ ሕይወትና ጉዳይ ልመና ማቅረብ

በዚህ ጸሎት ውስጥ አንድ ሰው ከእግዚአብሔር የሚያስፈልጉትን እርዳታዎች ሁሉ ለማጠቃለል ይችላል ። ዝርዝሩ ብዙ ነው ። ለምሳሌ :- ስለ ግል መንፈሳዊ ሕይወት ፥ ስለ ጤና ፥ ስለ ገንዘብ ፥ ስለ ትዳር ፥ ስላ አገልግሎት ፥ ስለ ሥራ ፥ ስለ ቤተሰብ ወዘተ ።

## ሐ/ ስለ ሌሎች ሰዎች መማለድ

ይህ የጸሎት ክፍል ሰፋ ያለ ነው ።

1ኛ/ ለልዩ ልዩ ሰዎች እንጸልያለን ። ግለ ሰብን ፥ ቤተሰብን ፥ ቤተ ክርስቲያኖችን ፥ ሕብረተሰብን ፥ ልዩ ልዩ ድርጅቶችን ፥ አገርን ፥ የዓለም አገሮችን ያጠቃልላል ።

2ኛ/ የሚጸለዩባቸዉም ጉዳዮች እጅግ ብዙ ናቸው ። ለምሳሌ :- ስለ ነፍሳት መዳን ፥ ስለ ፖለቲካ ፥ ስለ ኢኮኖሚ ፥ ስለ ጤና ፥ ስለ ሰላም ፥ ስለ ዝናብ ወዘተ ( 1ጢሞ 2:1-4 ) ።

እግዚአብሔርን ማምለክ በአራት ክፍሎች ይከፈላል ብለናል ። እነዚህም የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ ፥ እግዚአብሔርን ማወደስ ፥ እግዚአብሔርን ማመስገንና ወደ እግዚአብሔር መጸለይ ናቸው ።

ከእነዚህም መካከል እግዚአብሔርን ማወደስና እግዚአብሔርን ማመስገን ለዘላለም ጸንተው የሚኖሩ ናቸው ። በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከነገድና ከቋንቋ የተዋጁት ፥ የንጉሥ ካህናትና ቅዱስ ሕዝብ የሆኑት ሁሉ በተቀደሰው የእግዚአብሔር ዙፋን

ፊት ለዘላለም ሲያወድሱትና ሲያመሰግኑት ይኖራሉ ! ከዚህ እድል ፈንታ ተካፋዮች የሆኑ የተባረኩ ናቸው



# ምዕራፍ 8

## ችግረኞችን መርዳት

ምንም እንኳን ከዋነኞቹ መሠረታዊ የቤተ ክርስቲያን የተልእኮ ክፍሎች አንዱ ባይሆንም ፥ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ከመመለስና የምእመናንን መንፈሳዊ ሕይወት ከማነጽ ጋር የተያያዘ አንድ መዘንጋት የሌለብን ነገር አለ ። ይህም ጉዳይ ችግረኞችን መርዳት ነው ።

ችግረኞችን ስለ መርዳት ሁለት የተዛቡ አመለካከቶች አሉ ። አንዱ አመለካከት ፥ <u>ችግረኞችን መርዳት ላይ ብቻ ያተኩራል</u> ። ሌላው አመለካከት ደግሞ <u>ችግረኞችን መርዳት ምንም መንፈሳዊነት እንደሌለው በመቁጠር የነፍሳት ደህንነት ላይ ብቻ ያተኩራል</u> ።

በጠቅላላው የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ችግረኞችን መርዳት ብቻ ፥ ወይም ይበልጡን ችግረኞችን መርዳት እንደሆነ የሚያስመስሉ ሰዎች እጅግ በጣም ተሳስተዋል ። ሐዋርያ ጳውሎስ ክርስቶስ

የሞተበትን ዋና አላማ ሲገልጥ እንዲህ ይላል ፥ “ እኔ የተቀበልኩትን ፥ መጀመሪያ ደረጃ ያለዉን ነገር ለእናንተ አስተላለፍሁላችሁ ፤ ያስተላለፍሁላችሁም ነገር በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈው ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ ....” ( 1ቆሮ 15:3 ) ።

ስለዚህ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መመለስ ችግረኞችን ከመርዳት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ አለብን ። ይሁን እንጂ ችግረኞችን መርዳት መንፈሳዊነት የሌለው ነገር አድርገን ማየት ስህተት ይሆንብናል ። ምክንያቱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ችግረኞችን መርዳት የርሱ ፈቃድ መሆኑንና መንፈሳዊነት ያለው አገልግሎት እንደሆነ ግልጽ ባለ ሁኔታ በማቴ 25 :31-40 ገልጦታል ።

“ ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ የሰው ልጅ በመላእክት ሁሉ ታጅቦ በክብር ሲመጣ በክብር ዙፋኑ ላይ ይቀመጣል ፤ ሕዝቦች ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ ፤ እረኛ በጎችን ከፍየሎች እንደሚለይ እርሱም ሕዝቦችን ይለያል።

በጎቹን በቀኙ ፥ ፍየሎቹን በግራው ያቆማቸዋል ። በዚያን ጊዜ ንጉሡ በቀኙ በኩል ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል ። እናንተ አባቴ የባረካችሁ ፥ ኑ ! ዓለም ሲፈጠር ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ ፤ ምክንያቱም ተርቤ አብልታችሁኛል ፤ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛል ፤ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛል ፤ ታርዤ አልብሳችሁኛል ፤ ታምሜ ጠይቃችሁኛል ፤ ታስሬ ጎብኝታችሁኛል ።

በዚያን ጊዜ ጻድቃን እንዲህ ሲሉ ይመልሱለታል ፥ ጌታ ሆይ ! መቼ ተርበህ አየንህና አበላንህ ? መቼ ተጠምተህ አየንህና አጠጣንህ ? መቼ እንግዳ ሆነህ አየንህና ተቀበልንህ ? መቼ



ታርዘህ አየንህና አለበስንህ ? መቼ ታመህ ወይም ታስረህ አየንህና ጠየቅንህ ? ንጉሡም በእውነት እላችኋለሁ ፥ ከእነዚህ ከወንድሞቼ አነስተኛ ለሆነው ለአንዱ እንኳ ያደረጋችሁት ሁሉ ለእኔ እንዳደረጋችሁት ነው ሲል ይመልስላቸዋል ። ”

ይህ ቃል የእግዚአብሔር ልጅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው ቃል ነው ። ስለ ቃሉ ደግሞ ሲናገር እንዲህ ይላል ። “ ሰማይና ምድር ያልፋሉ ፤ ቃሌ ግን ለዘላለም ይኖራል ” ( ማቴ 24 ፡ 35 ) ። ስለዚህ ይህ የጌታችን ትምህርት ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዓለም እስካለች ድረስ በተግባር መገለጽ ያለበት ትምህርት ነው ።

በሐዋርያት ዘመን የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ይህን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርት እንዴት አየችው ? የችግረኞችን ጉዳይ እንዴት ተመለከተችው ? ስለዚህ ጉዳይ ከሐዋርያ ጳውሎስ የበለጠ የሚረዳን ስለሌለ የእርሱን አገልግሎትና አመለካከት ይንገረን።

1 ቆሮ 16 ፡ 1-4 :-

“ለምእመናን ስለሚደረገው የገንዘብ መዋጮ ለገላትያ አብያተ ክርስቲያናት በሰጠሁት መመሪያ መሠረት እናንተም እንዲህ አድርጉ ። እኔ በምመጣበት ጊዜ የገንዘብ መዋጮ እንዳይደረግ ፥ በየሳምንቱ እሁድ ከእናንተ እያንዳንዱ በሚያገኘው ገቢ መጠን እያዋጣ ለይቶ ያስቀምጥ ። እኔ ወደ እናንተ በምመጣበት ጊዜ እናንተ የምትመርጡዋቸዉን ሰዎች ፥ ያዋጣችሁትን ገንዘብ ይዘው ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄዱ ከመሸኛ ደብዳቤ ጋር እልካቸዋለሁ ።የእኔም መሄድ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ አብረዉኝ ይሄዳሉ። ”

ሐዋርያ ጵውሎስ ይህን መመሪያ የሰጠው በመጀመሪያው መልእክቱ እንደሆነ ግልጽ ነው ። እስቲ ጳውሎስ ይህን ችግረኞችን የመርዳት ጉዳይ ምን ክብደት እንደሰጠውና በምን ሁኔታ እንደተከታተለው በሁለተኛው መልእክቱ ውስጥ እንመልከት ።

2 ቆሮ 9፡1-5 :-

“ በይሁዳ ላሉት ክርስቲያኖች ስለሚደረገው መዋጮ ልጽፍላችሁ አያስፈልግም ፤ እናንተ በአካይያ ያላችሁ ሰዎች ለዕርዳታ ያላችሁን በጎ ፈቃድ በማወቄ የአካይያ ስዎች ከአምና ጀምሮ ለመርዳት ዝግጁዎች ናቸው ብዬ ለመቄዶንያ ሰዎች በትምክህት ተናግሬአለሁ ። እንዲያውም እናንተ ለመርዳት ያላችሁ ፍላጎት አብዛኞዎቹም እንዲረዱ አድርጎአቸዋል ። በዚህ ነገር በእናንተ ላይ ያለን ትምክህት ከንቱ ሆኖ እንዳይቀር እነዚህን ወንድሞች እልካለሁ ፤ እናንተም ልክ ከዚህ በፊት እንዳልኩት ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ ። የመቄዶንያ ሰዎች ከእኔ ጋር ወደ እናንተ መጥተው ያልተዘጋጃችሁ ሆናችሁ ቢያገኙዋችሁ በእናንተ በመመካታችን እናፍራለን ፤ እናንተማ በጣም ታፍራላችሁ ። ስለዚህ ልትሰጡ ቃል የገባችሁበትን በቅድሚያ እንድታዘጋጁ እንዲያስታዉሱአችሁ በማለት እነዚህ ወንድሞች ከእኔ ቀድመው ወደ እናንተ እንዲመጡ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቻለሁ ። በዚህ ዓይነት እኔ በምመጣበት ጊዜ ስጦታችሁ ዝግጁ ይሆናል ፤ እናንተም የምትሰጡት በግድ ሳይሆን በፈቃደኝነት መሆኑን ያሳያል ። ”

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው ሐዋርያው ጳውሎስና በሐዋርያት ዘመን የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ችግረኞችን የመርዳት ጉዳይ በክብደት ነው የወሰዱት ። ይህም ማለት ጌታችን ያስተማረውን



ትምህርት በትኩረት ወስደዉታል ማለት ነው ። ስለዚህ ችግረኞችን መርዳት ለቤተ ክርስቲያን የምርጫ ጉዳይ አይደለም ።

ቤተ ክርስቲያን ቅድሚያ መስጠት ያለባት ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ለመመለስና የምእመናንን መንፈሳዊ ሕይወት ለማዳበር ነው ።

ይሁን እንጂ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ስትመልስ ሆነ የምእመናንን መንፈሳዊ ሕይወት ስታንጽ ፣ እንደ ጊዜው ሁኔታና እንደ አቅሟ ችግረኞችን መርዳት መዘንጋት የለባትም ።

እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ችግረኞችን የመርዳት ጉዳይ ለነፍስ ደህንነት ወንጌልን ከመስበክ የሚቀድምበት ጊዜ ይኖራል ። ለምሳሌ :- ሰው አካሉ ተቆርጦ ለሕይወቱ በሚያሰጋ ሁኔታ ደሙ እየፈሰሰ ብናየው ፣ ለነፍሱ ደህንነት ወንጌልን ከመስበክ ይልቅ ደሙን የማቆም ጉዳይ መቅደም አለበት ። እንዲሁም ሰው ቤቱ በእሳት ተቃጥሎ ወይም በጎርፍ ተጥለቅልቆ ወይም በመኪና ተገጭቶ ብናየው ፣ ለነፍሱ ደህንነት ወንጌልን ከመስበክ ይልቅ ሰውየውን በችግሩ መርዳት መቅደም አለበት ።

ሰለዚህ ቤተ ክርስቲያን ፣ እንደ ጊዜው ሁኔታና እንደ አስፈላጊነቱ ፣ እንዲሁም እንደ አቅሟ ችግረኞችን መርዳት አለባት ። ችግረኞችን መርዳት መንፈሳዊነት አለው ።

# ምዕራፍ 9

## በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ

የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መድረክ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ መሆን አለበት ። አስፈላጊነቱ የሚያጠያይቅ ጉዳይ አይደለም ። ይሁንና በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ ምን ይመስላል ? በምን ይታወቃል ? በምንስ ይመዘናል ? ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ ወንጌል 6:44 "ዛፍ ሁሉ በፍሬው ይታወቃል " ብሎ እንደተናገረው ፣ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ የሚመዘነው በአገልግሎቱ ፍሬ ነው ።

በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ ማሳየት ከሚገባቸው ፍሬዎች ማካከል ዋና ዋናዎቹን ከዚህ ቀጥዬ እዘረዝራለሁ ።

## ነፍሳትን ወደ እግዚአብሔር ይመልሳል

ለማቀርበው አሳብ የእግዚአብሔርን ቃል መሠረት ለማደረግ እፈልጋለሁ ። ስለዚህ የዘመኑን ልዩ ልዩ መድረኮች እንደ ምሳሌ ለማቅረብ ከመሞከር ይልቅ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እንድንመለከት



ያስፈልጋል ። ምክንያቱም ትክክለኛው ሚዛንና ፈራጅ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው ።

እስቲ የሐዋርያትን መድረክ እንመልከት ። " በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ ከአሥራ አንዱ ጋር ቆመና ድምጹን ከፍ አድርጎ ለሕዝቡ እንዲህ ሲል ተናገረ ..... እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታና መሲሕ እንዳደረገው የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ በእርግጥ ይወቅ "ሰዎቹም ይህን በሰሙ ጊዜ ልባቸው በሐዘን ተነክቶ ጴጥሮስንና ሌሎቹን ሐዋርያት " ወንድሞች ሆይ ! እንግዲህ ምን እናድርግ ? " አሉአቸው ።

ጴጥሮስም እንዲህ አላቸው " ንስሐ ግቡ ፤ ኃጢአታችሁም ይቅር እንዲባልላችሁ እያንዳንዳችሁበኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ ፣ የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነውን መንፈስ ቅዱስንም ትቀበላላችሁ ......ከእነርሱም ብዙዎቹ ቃሉን ተቀብለው ተጠመቁ ፤ በዚያን ቀን ሶስት ሺህ የሚያህሉ አማኞች ተጨመሩ " ( የሐ ሥ 2:14 ፣ 36-38 ፣ 41 ) ።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንደምንመለከተው በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ የመድረክ አገልግሎት ነፍሳትን ወደ አምላካቸው ይመልሳል ። መድረካችን ነፍሳትን ወደ አምላካችን የማይመልስ ከሆነ ቆም ብለን የመድረካችንን አገልግሎት መመዘን አለብን ። ምክንያቱንም መፈለግ አለብን ። በአንድ መልእክት ሶስት ሺህ የሚያህሉ ነፍሳት ወደ ጌታ ይመለሳሉ ማለት አይደለም ። ይሁን እንጂ የሚድኑት በየሳምንቱ ፣ ካልሆነም በየወሩ ወደ ጉባኤያችን መጨመር አለባቸው ።

ሐዋርያትና ሌሎችም አገልጋዮች " ከጸለዩ በኋላ የነበሩበት

ስፍራ ተናወጠ ፤ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ ፤ የእግዚአብሔርንም ቃል ያለ ፍርሃት በድፍረት ተናገሩ ” ( የሐ ዋ 4:31 ) ። በዚህ ሁኔታ መድረካቸው በእግዚአብሔር ቃል ፥ በጸሎትና በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ እንዲሆን ይተጉ ነበር ። “ እኛ ግን በመጸለይና የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር እንተጋለን ” በማለት ቆረጡ ( የሐ ሥ 6:4 ) ።

ውጤቱስ ምን ሆነ ? ነፍሳት በብዛት ወደ እግዚአብሔር ይመለሱ ነበር ። “ በዚህ ሁኔታ የእግዚአብሔር ቃል እየተስፋፋ ስለ ሄደ በኢየሩሳሌም የአማኞች ቁጥር በጣም እየበዛ ሄደ ፤ ከካህናትም ብዙዎች አመኑ ” ( የሐ ሥ 6:7 ) ።

በመንፈስ ቅዱስ የተሞላው የጳውሎስ የአገልግሎት መድረክ ብዙዎቹን የተሰሎንቄን ሰዎች “ ሕያውና እውነተኛ የሆነዉን አምላክ ለማገልገል ከጣዖቶች ወደ እግዚአብሔር ” መለሳቸው ( 1ተሰ 1:5-9 ) ። በአንጾኪያ የተመሠረተው በመንፈስ ቅዱስ የተሞላው የአገልግሎት መድረክ የከተማዉን ሕዝብ ከድቅድቅ ጨለማ ወደሚደነቀው የእግዚአብሔር ብርሃን እንደመለሰ ተጽፎ እናነባለን ( የሐ ሥ 11:20-24 ) ።

ጳውሎስ አስራ ሁለት ሰዎችን ይዞ በኤፌሶን ከተማ የመሠረተው የአገልግሎት መድረክ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ ነበር ። ከዚህ የተነሳ ቀደም ሲል አርጤሚስ ለምትባል ጣኦት ይገዙ የነበሩት ብዙ ነፍሳት ወደ እውነተኛው አምላካቸው ተመለሱ ። ሕይወት ያለበትና የጨለማንም ሥራ የሚያፈርስ አገልግሎት በዚህ ከተማ ተስፋፋ ።

በአርጤሚስ አማካይነት በኤፌሶን ከተማ የሚሠራዉን



“ የዲያቢሎስን የተንኮል ሥራ ” ለመቃወምና ምርኮን ለመበዝበዝ የሚችል ጉባኤ ተመሠረተ ( ኤፌ 6:10-19 ) ።

ስለዚህ ጉዳይ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍሎች ጨምሮ እንደ መረጃ ለማቅረብ ይቻላል ። ነገር ግን ለምሳሌ ያህል እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት መረጃዎች በቂ ናቸው ። ይህ በሐዋርያት ዘመን ብቻ የተደረገና በዚህ ዘመን ሊደገም የማይችል ነገር አይደለም ። ይህ የማይለወጥ ለሁልጊዜ የሚኖር የእግዚአብሔር መለኮታዊ አሠራር ነው ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቻ ተጠቅሶ የምንመለከት ጉዳይም አይደለም ። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ፥ እንዲሁም በዘመናችን ሲደጋገምና ሲገለጽ የምናየው መለኮታዊ አሠራር ነው ።

ስለዚህ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ ከሚታወቅባቸው ነገሮች አንዱ የነፍሳት በብዛት ወደ እግዚአብሔር መመለስ ነው ። ይህ ምልክትና መለኮታዊ አሠራር የማይታይበት መድረክ ፥ በጾምና በጸሎት መመርመር ይገባዋል ። ይህ ችግር እስኪስተካከል ድረስ መተኛት የለብንም ።

## ምእመናንን የተሰጡ ያደርጋል

መድረካችን በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ከሆነ ምእመናን ያለ መቆጠብ የተሰጡ ይሆናሉ ። ይህ ሚዛን ሁለተኛው ሚዛን መሆን አለበት ። ሰዎች ከኃጢአት ኑሮ ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ ለኃጢአታቸው ይቅርታ ማግኘት አንድ ነገር ነው ። ነገር ግን ወደ ሕያው እግዚአቢሔር ከተመለሱ በኋላ የተሰጡ ምእመናን

ሆነው በእግዚአብሔር ቤት መኖር ሌላ ጉዳይ ነው ። መታወቅ ያለበት ነገር ለምእመናን የመስጠት ጉዳይ የምርጫ ጉዳይ እንዳልሆነ ነው ።

መስጠት ሲባል ምን ማለት ነው ? የምንሰጠውስ ለማን ነው ? ለምንድነው ? እያንዳንዱ ምእመን ሶስት ዓይነት መስጠት መስጠት አለበት ። እነዚህን ሶስት ዓይነት መስጠት ከዚህ ቀጥዬ እዘረዝራለሁ ።

## ለእግዚአብሔር መስጠት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያዎቹን አማኞችና አገልጋዮች ሲጠራ የተጠቀመበት ዓረፍተ ነገር " ኑ ተከተሉኝ " የሚል ነበር ( ማቴ 4:18-22 ) ። እነርሱም ይህን ቃል ከሰሙ በኋላ ተቀብለው " ተከተሉት " ( ማቴ 4:20፥22 ) ።

ኢየሱስ ይህን አጠራር ሁልጊዜ ይጠቀምበት ነበር ። ለምሳሌ እነጴጥሮስን በዚህ መንገድ ከጠራ በኋላ ብዙ ጊዜ ቆይቶ ቀረጥ ሰብሳቢውን ማቴዎስን ቀረጡን እየሰበሰበ ሳለ አገኘው ። " ኢየሱስም ...... ማቴዎስ የተባለዉን ቀራጭ በቀረጥ መቀበያ ስፍራ ተቀምጦ አየውና ተከተለኝ " አለው ። " ማቴዎስ ተነሥቶ ተከተለው " ( ማቴ 9:9 ) ።

" መከተል " የመስጠት ምልክት ነው ። መከተል ወይም መስጠት ከሁሉም ነገር ይቀድማል ። መከተል ወይም መስጠት እግዚአብሔርን ማገልገልን እንኳ ይቀድማል ። አገልግሎት ትርጉም የሚኖረው ፥ ፍሬያማ የሚሆነውና እግዚአብሔርን የሚያስደስተው



መስጠት ሲቀድመው ነው ። ጌታችን ኢየሱስ ይህን መሠረታዊ ነገር ከዚህ እንደሚከተለው በማስቀመጥ ግልጽ አድርጎታል ፤ " እኔን ማገልገል የሚፈልግ ይከተለኝ " ( ዮሐ 12:26 ) ።

በስም ብቻ መከተል ወይም " ጌታ ሆይ ! ጌታ ሆይ ! " ማለት ብቻ በቂ አይደለም ። በሙሉ ልብ መስጠት አስፈላጊ ነው ። ከዚህ ያነሰ ነገር ጌታን አያስደስተውም ። ተቀባይነትም አይኖረውም ። በዚህ ጉዳይ እንዳንታለል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግልጥ አድርጎ ተናግሮታል ።

" ብዙ ሰዎች ከኢየሱስ ጋር አብረው ይሄዱ ነበር ፤ እርሱም ወደ እነርሱ መለስ ብሎ እንዲህ አላቸው ፥ ወደ እኔ የሚመጣ ሁሉ አባቱንና እናቱን ፥ ሚስቱንና ልጆቹን ፥ ወንድሞቹንና እህቶቹን ፥ የራሱንም ሕይወት እንኳ ከእኔ አብልጦ የሚወድ ከሆነ የእኔ ደቀ መዝሙር ሊሆን አይችልም " ( ሉቃ 14:25-26 ) ።

" መስጠት " የሚለዉን ቃል ከዚህ በበለጠ መንገድ ለመግለጥ አይቻልም ። መስጠት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ከባለቤቱ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የበለጠ ለመግለጥ የሚችል አዋቂ አይገኝም ።

እነዚህን ጥቅሶች ስንመለከት መገንዘብ ያለብን ነገር አለ ። ይኸውም ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተሰባችንን እንዳንወድ አልተናገረም ። ጠላታችንንም እንኳ እንድንወድ አዝዞናል ። ራሳችንንም እንዳንወድ አልተናገረም ። ራሳችንን እንደምንወድ ጎረቤታችንንም እንድንወድ አስተምሮናል ።

ETHIOPIAN ... CHURCH
9... RD.
DALLAS, TX 75218

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትኩረት እንድንሰጠው የፈለገው ነጥብ " ከእኔ አብልጦ " የሚለዉን ቃል ነው ። ይህም ማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በትዳራችንም ፥ በሥራችንም ፥ በንግዳችንም ፥ በእርሻችንም ፥ በትምህርታችንም ፥ በኑሮአችንም ሁሉ የመጀመሪያውን ስፍራ መያዝ አለበት ማለት ነው ።

በመንፈስ ቅዱስ በተሞላ የመድረክ አገልግሎት ወደ ሕያው እግዚአብሔር ስለተመለሱት የተሰሎንቄ ምእመናን ቀደም ብዬ ጠቅሼ ነበር ። በእነዚህ ምእመናን የሚታየው የሕይወት ፍሬ ከጣኦቶች ወደ እግዚአብሔር መመለስ ብቻ አይደለም ። እነዚህ ምእመናን ለእግዚአብሔርም የተሰጡ ምእመናን ነበሩ ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ እነዚህ ምእመናን ሲመሰክር እንዲህ ይላል ፥ " ወንድሞች ሆይ ! እግዚአብሔር በመቄዶንያ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት የሰጠውን ጸጋ እንድታውቁ እንወዳለን ። እነርሱ ብዙ መከራና ፈተና ደርሶባቸዋል ፤ ይሁን እንጂ ደስታቸው ታላቅ ስለሆነ ምንም እንኳ በጣም ድሆች ቢሆኑም ከፍ ያለ ልግስና አድርገዋል ። የሚቻላቸዉን ያህል ብቻ ሳይሆን ከሚቻላቸውም በላይ በፈቃደኝነት እንደሰጡ እኔ እመሰክርላቸዋለሁ ፤ በይሁዳ ያሉትን ክርስቲያኖች የመርዳት እድል እንዳይነፈጋቸው አጥብቀው ለመኑን ፤ እነርሱ ያደረጉት እኛ ከጠበቅነው በላይ ነው ፤ በመጀመሪያ ራሳቸውን ለጌታ ሰጡ ፤ ቀጥለውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን ለእኛ ሰጥተዋል " ( ቆሮ 8:1-5 ) ።

ተሰሎንቄ የሚገኘው መቄዶንያ ተብሎ በሚጠራው ክፍለ አገር ውስጥ ነው ። ስለዚህ ጳውሎስ " በመቄዶንያ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት " ሲል የተሰሎንቄንም ቤተ ክርስቲያን ጨምሮ ነው ። እንዲያውም ስለ ተሰሎንቄ ምእመናን ሲመሰክር ፥ "



ምንም እንኳ ብዙ መከራ ቢደርስባችሁም ከመንፈስ ቅዱስ በተገኘ ደስታ ቃሉን ተቀብላችሁ እኛንና ጌታ ኢየሱስን የምትመስሉ ሆናችኋል ። ስለዚህ በመቄዶንያና በአካይያ ለሚገኙት ምእመናን ሁሉ መልካም ምሳሌ ሆናችኋል " በማለት ገልጿል ( 1ተሰ 1:6-7 ) ።

ሐዋርያ ጳውሎስ የተሰሎንቄ ምእመናን እርሱና የአገልግሎት ባልደረቦቹ ከጠበቁዋቸው በላይ ሆነውና አድርገው የተገኙበትን ዋና ቁልፍ ነገር ሲጠቅስ እንዲህ ይላል ፥ " በመጀመሪያ ራሳቸውን ለጌታ ሰጡ " ( 1ቆሮ 8:5 ) ። አንድ ምእመን " ባመጀምሪያ ራሱን ለጌታ " ከሰጠ ሌሎች ነገሮች አስቸጋሪ አይሆኑበትም ። ይህም ማለት አስቀድሞ ራሱን ለጌታ ከሰጠ ገንዘቡን ለጌታ መስጠት አያስቸግረውም ። በመጀመሪያ ራሱን ለጌታ ከሰጠ አገልግሎቱን ለጌታ መስጠት አይከብደውም ። ጊዜውን ለጌታ መስጠት አይከብደውም ።

ምክንያቱም ራሱም ፥ ገንዘቡም ፥ እውቀቱም ፥ ጉልበቱም ፥ ንግዱም ፥ እርሻውም፥ ቤተሰቡም ፥ የእርሱ የሆኑት ሁሉ የጌታ መሆናቸው ነው ። እንደዚህ ዓይነቶቹን ምእመናን ለማፍራት የሚቻለው በመንፈስ ቅዱስ በተሞላ መድረክ ነው ። የመድረካችን ፍሬ ከዚህ የተለየ ከሆነ በጥሞና መድረካችንን መመዘን አለብን ። ለምን ራሳቸዉን ለጌታ የሰጡ ምእመናን ማፍራት አቃተን ? ከምን የተንሣ ነው ? በእውነት መንፈስ ፥ በጾምና በጸሎት መድረካችንን ከፈተሽን ፥ ከመዘንን ጌታን ከጠየቅን መልስ ልናገኝ እንችላለን ። ምክንያቱም በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ ራሳቸውን ለጌታ የሰጡ ምእመናን እንደሚያፈራ የታወቀና የተረጋገጠ ነው።

አንድ ነገር እንዳንዘነጋ ላሳስብ እወዳለሁ ። ይኸውም

መድረካችን በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሆኖ እያለ ራሳቸዉን ለጌታ በሙሉ ለመስጠት የማይፈቅዱ ይኖራሉ ። ስለዚህ እንደነዚህ ባሉት ምእመናን ምክንያት ሰይጣን እንዳይከስን መጠንቀቅ አስፈላጊ ነው ። ይሁን እንጂ መድረካችን በመንፈስ ቅዱስ ከተሞላ የሚበዙቱ ምእመናን ራሳቸውን ለጌታ የሰጡ ይሆናሉ ። በዚህ መጠራጠር የለብንም ።

## ለእግዚአብሔር ሕዝብ መስጠት

በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ ለእግዚአብሔር የተሰጡትን ምእመናን እንደሚያፈራ ተመልክተናል ። ይህ የመጀመሪያውና ዋነኛው መስጠት ነው ። ይህ ብቻ በቂ አይደለም ። ሌላም መስጠት አለ ። ይህ ሁለተኛው መስጠት ነው ። ሁለተኛው መስጠት አንድ አማኝ ራሱን ለእግዚአብሔር ሕዝብ የሚሰጠው መስጠት ነው ።

አማኝ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ባለው ሕብረት መሠረት ከሌሎች ምእመናን ጋር እንደ አካል ክፍል የተያያዘና የተገጣጠመ ነው ። ስለዚህ አስገራሚ የእግዚአብሔር ሥራ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይጽፋል ፤ “ በአንዱ አካላችን ብዙ ክፍሎች አሉ ፤ እያንዳንዱም የአካል ክፍል የተለየ ሥራ አለው ። እንዲሁም እኛ ብዙዎች ሆነን ሳለን በክርስቶስ አንድ አካል ነን ፤ የአንድ አካል ክፍሎች እንደመሆናችንም መጠን እርስ በርሳችን ተገጣጥመናል ” ( ሮሜ 12:4-5 ) ።

ከእነዚህ ጥቅሶች እንደምንረዳው አንድ አማኝ ክርስቲያን



በመሆኑ ብቻ የሌሎች ክርስቲያኖች የአካል ክፍል ነው ። ይህ ሁኔታ አንድ ምእመን ለሌሎች ምእመናን የተሰጠ መሆኑን ያሳያል ። ይህ መሰጠት መንፈሳዊ መሰጠት ነው ።

ይሁን እንጂ ይህ መንፈሳዊ መሰጠት በተግባር ካልተገለጠ እውነተኛ መሰጠት አይሆንም ። በዚህ ክፍል ልጠቅሰው የፈለግሁት መሰጠት በዚህ መንፈሳዊ መሰጠት ላይ ተመሥርቶ ተግባራዊና በዓይን የሚታየውን መሰጠት ነው ። ምክንያቱም አንድ ምእመን በመንፈሳዊ አሠራር ለሌሎች ምእመናን የተሰጠ ሆኖ እያለ በተጨባጭ ሁኔታ በተግባራዊ መሰጠት ላይሰጥ ይችላል ።

ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ ምእመናን ለምእመናን በተግባራዊ ሁኔታ የተሰጡ እንዲሆኑ ያደርጋል ። ይህ ዓይነቱ መሰጠት በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ የሚያስገኘው ፍሬ ነው ። ይህ ዓይነቱ ተግባራዊ መሰጠት ለሌሎችም ምእመናን መኖር ማለት ነው ። ይህ ዓይነቱ መሰጠት ለሌሎች ምእመናን በረከት መሆን ማለት ነው ።

አማኞች ለሌሎች አማኞች ስለመሰጠት ጉዳይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በልዩ ልዩ ቃላት ፥ አነጋገርና ገለጻ ተጠቅሶ እናገኛለን ። ከብዙዎች መካከል አንዳንዶቹን ከዚህ ቀጥዬ እጠቅሳቸዋለሁ።

### 1ኛ/ ሌሎችን ምእመናን ማገልገል ነው

ለሌሎች ምእመናን የተሰጠ እውነተኛ አማኝ ሌሎችን ምእመናን ያገለግላል ። ስለዚህ ጉዳይ ሐዋርያ ጳውሎስ እንዲህ ይላል ፤ “ ወንድሞቼ ሆይ ! እናንተ ለነፃነት ተጠርታችኋል

፤ ነገር ግን አንዱ ሌላውን በፍቅር ያገልግል እንጂ ይህ ነፅነታችሁ የሥጋን ምኞት መፈጸሚያ ምክንያት አይሁን "( ገላ 5:13 )።

ለሌሎች ምእመናን የተሰጡ ምእመናን ሌሎችን ምእመናን ያገለግላሉ ማለት ነው ። በተጨማሪም ፣ የተሰጡ ምእመናን ከሆኑ ለሌሎች ምእመናን የሚሰጡት አገልግሎት በፍቅር የተገፋፋና በፍቅር የተለወሰ አገልግሎት ይሆናል ። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል የሚያዘን " አንዱ ሌላዉን ያገልግል " አይልም ። " አንዱ ሌላውን በፍቅር ያገልግል " ነው የሚለው ።

የተሰሎንቄ ምእመናን ለክርስቶስ የተሰጡ ምእመናን መሆናቸውን ቀደም ብለን ተመልክተን ነበር ። እነዚህ ምእመናን ለክርስቶስ ብቻ አልነበረም የተሰጡት ። ለሌሎችም ምእመናን ነበር የተሰጡት ። ሐዋርያ ጳውሎስ " በመጀመርያ ራሳቸውን ለጌታ ሰጡ " ካለ በኋላ " ቀጥሎም በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን ለእኛ ሰጥተዋል " ሲል ይመሰክርላቸዋል ( 2ቆሮ 8:5 ) ።

የተሰንሎቄ ምእመናን ለሌሎች ምእመናን መሰጠት ተግባራዊ ነበር ። ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ እንደሚመሰክርላቸው ፣ " በብዙ መከራና ፈተና " እያለፉ ፣ " በጣም ድሆች " ሆነው እያሉ ፣ " በይሁዳ ያሉትን ክርስቲያኖች የመርዳት እድል እንዳይነፈጋቸው አጥብቀው " ለመኑ ( 2ቆሮ 8:3፥4 ) ። ይህ ብቻ አይደለም ። " የሚቻላቸውን ያህል ብቻ ሳይሆን ከሚቻላቸውም በላይ በፈቃደኝነት " ሰጡ ( 2ቆሮ 8:3 ) ። በተጨማሪም " እነርሱ ያደረጉት " ሐዋርያት የጠብቁባቸውን ሳይሆን እነርሱ ከጥበቁት በላይ ነበር ( 2ቆሮ 8:5 ) ።

በተጨባጭ ሁኔታ ለሌሎች ምእመናን መሰጠት ማለት



ይህ ነው ። ሳይለመኑ ራሳቸው በፍቅር ተገፋፍተውና ለምነው ሌሎችን ምእመናን በአስፈላጊ ሁኔታ አገለገሉ ።

ጳውሎስ በሮም የሚገኙትን ምእመናን ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሁኔታ ይመክራል ፣ " አማኞች ወንድሞችን በችግራቸው እርዱ ፤ በእንግድነት የሚመጡትንም ተቀበሉ ......ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ ፤ ከሚያለቅሱም ጋር አልቅሱ " ( ሮሜ 12:13 ፥ 15 )። ይህ ድርጊት ለሌሎች ምእመናን መሰጠትን ያመለክታል ። " አንድ ነን በመንፈሱ " ብሎ መዘመር ብቻ ሳይሆን ይህን አንድነት ፣ ይህን መሰጠት በተግባር ማሳየት አስፈላጊ ነው ። ሌሎችን ምእመናን ማገልገል በዚህ መንገድ ብቻ ሳይሆን በልዩ ልዩ መንገዶች ሊገለጥ ይችላል ። መገለጥም ይገባዋል ። ቁም ነገሩ የአገልግሎቱ ዓይነትና የአሰጣጡ መንገድ ሳይሆን ማገልገሉ ነው ።

## 2ኛ/ ሌሎችን ምእመናን ማነጽ ነው

ለሌሎች የተሰጠ አማኝ ስለ ሌሎች ምእመናን እድገት ማሰብ ይኖርበታል ። ማሰብ ብቻ አይበቃም ። በተጨባጭ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ ይገባዋል ። ምእመናን እርስ በርስ እንዲተናነጹ የእግዚአብሔር ምኞት ነው ። " ስለዚህ አሁን በምታደርጉት ዓይነት አንዱ ሌላውን በማነጽ እርስ በርሳችሁ ተረዳዱ " ( 1ተሰ 5:11 ) ።

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው እያንዳንዱ ምእመን ሌላውን ምእመን የማነጽ ሐላፊነትና እድል ፈንታ አለው ። " ማነጽ

" የሚለው ቃል መገንባትን ፣ ማሳደግን ፣ ማለምለምንና ፍሬያማ ማድረግን ያመለክታል ።

የተሰሎንቄ ምእመናን ለጌታ ኢየሱስ የተሰጡና ለሌሎችም ምእመናን የተሰጡ መሆናቸውን ተመልክተን ነበር ። መሰጠታቸውም በተግባር የተገለጠ መሆኑን አይተናል ። ከዚህ በላይ በተጠቀሰው በ1 ተሰ 5:11 " አሁን በምታደርጉት ዓይነት " እርስ በርስ ተናነጹ ሲል ጳውሎስ ይመክራቸዋል ። እነዚህ ምእመናን እርስ በርስ መተናነጽ ሐላፊነታቸው መሆኑን የተገነዘቡ ፣ ይህን መተናነጽ በተግባር እያሳዩ እንዳሉ ያመለክታል ።

የመተናነጽ ሐላፊነትና እድል ፈንታ ለተሰሎንቄ ምእመናን ብቻ የተሰጠ ነገር አይደለም ። ይህ ሐላፊነትና እድል ፈንታ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ የተሰጠ ፣ ከሁሉም ምእመናን የሚጠበቅ አሠራር ነው ። ስለዚህ ጉዳይ የእግዚአብሔር መንፈስ በጳውሎስ አፍ እንዲህ ሲል ይናገራል ፣ " ከቶ ከአፋችሁ ክፉ ቃል አይውጣ ፤ ነገር ግን ለሚሰሙት ጸጋን የሚሰጥና ለማነጽ የሚጠቅም ፣ ለሰዎች አስፈላጊ የሆነውን ቃል ተናገሩ " ( ኤፌ 4:29 ) ።

ምእመናን ለምእመናን የተሰጡ ከሆኑ የማነጹ ጉዳይ በአንድ አቅጣጭ ብቻ የሚደርግ ነገር አይደለም ። በሁለቱም አቅጣጫዎች የሚደርግ ጉዳይ ነው ። ይህም ማለት እያንዳንዱ አማኝ ከራሱ አልፎ ለሌሎች ሲኖር " እርስ በርስ " የሚለው ቃል ተግባራዊ ይሆናል ። ሁሉም ያንጻል ፣ ሁሉም ይታነጻል ። ይህ መሰጠትን ያመለክታል ።

" ስለዚህ ሰላም የሚገኝበትንና እርስ በርሳችን የምንተናነጽበትን



ነገር እንከተል " (ሮሜ 14:19) ። ጳውሎስም እንኳ ለሌሎች ምእመናን የተሰጠና ሌሎች ምእመናንም ለእርሱ የተሰጡ መሆናቸውን በማመልከት " እርስ በርሳችን " በሚል ቃል ሲጠቀም እናያለን ። እንግዲህ እንደተመለከትነው ለእግዚአብሔር የተሰጡ ምእመናን ሌሎችን ተግባራዊ ተጨባጭ በሆነ ሁኔታ ለማነጽ ፣ ለማሳደግ ፣ ለመገንባትና ለማለምለም ይኖራሉ ። በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ ብቻ ነው እንደ እነዚህ ያሉትን ምእመናን ለማፍራት የሚችለው ። የሚተናነጹና የሚገነባቡ ምእመናን በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ ፍሬ ናቸው ።

## 3ኛ/ ሌሎችን ምእመናን ማበረታታት

እቃ በእጃችን ተሸክመን ስንሄድ አንዱ እጅ ሲደክም ሌላው እጅ ሳይለመንና ሳይታዘዝ ቶሎ ብሎ ያንን የደከመውን እጅ ሲረዳ ይታያል ። እጅ እርዳት እንደሚያስፈልግና ያንን እርዳት ከሌላው እጅ እንደሚያገኝ ሁሉ አማኝም መበረታታት የሚያስፈልግበት ጊዜ ይኖራል ።

ለዚህ ነው አንዱ የአካል ክፍል ለሌሎች የአካል ክፍሎች የተሰጠው ። "አንዱ የአካል ክፍል ሲሠቃይ ሌሎችም የአካል ክፍሎች በሙሉ አብረው ይሠቃያሉ ፤ አንዱ የአካል ክፍል ሲከበር ሌሎችም የአካል ክፍሎች አብረው ከእርሱ ጋር ይደሰታሉ። "

" እናንተም እኮ የክርስቶስ አካል ናችሁ ፤ እያንዳንዳችሁም የአካሉ ክፍሎች ናችሁ " ( ቆሮ 12:26-27 ) ። ይህን እውነት በአእምሮ ማወቅ አንድ ነገር ነው ። ነገር ግን አውቆ በተግባር

ማሳየት ሌላ ጉዳይ ነው ። ራሱን ለሌሎች ምእመናን የሰጠ ሰው ብቻ ነው መሰጠቱን በትግባር የሚያሳይ ።

ድካማቸው ላይ በማተኮርና ብቃት የሌላቸው እየመሰላቸው “ እኛ ለማንም አናስፈልግም ” የሚሉትን ምእመናን ፥ እግዚአብሔር ፥ “ ለማንም አናስፈልግም አትበሉ ፤ እናንተም ለሌሎች ሁሉ ምእመናን ታስፈልጋላችሁ ” ይላቸዋል ።

እንደዚሁም ብርታታቸው ላይ በማተኮር የሌሎች ምእመናን ማበረታታት የማያስፈልጋቸው የሚመስላቸውን ምእመናን ፥ እግዚአብሔር “ አትታበዩ ፥ የሌሎች ምእመናን ማበረታታት ለእናንተም ያስፈልጋችኋል ” ይላቸዋል ።

“ ዘወትር እየተገናኘን እርስ በርሳችን እንበረታታ እንጂ አንዳንዶች ማድረግ እንደለመዱት መሰብሰባችንን አንተው ፤ ይልቁንም የጌታ መምጫ ቀን መቃረቡን እያስታወሳችሁ ይህን ነገር በይበልጥ አድርጉ ” ( ዕብ 10:25 ። “ እርስ በርሳችን እንበረታታ ” የሚለው ቃል በአእምሮ አውቆ በልብ የሚታመንበት ብቻ አይደለም ። በአእምሮ አውቀን ፥ በልብ አምነን በተጨባጭ ሁኔታ ተግባራዊ የምናደርገው መለኮታዊ መመሪያ ነው ።

ሳይገደዱ ፥ ሳይገፋፉ ፥ ለማስመሰል ሳይሆን ፥ ከልባቸው አምነውበት ፥ በተጨባጭ ሁኔታ ሌሎችን ምእመናን የሚያበረታቱ ምእመናን በእውነት ለሌሎች ምእመናን የተሰጡ ምእመናን ናቸው ። ለእግዚአብሔር ሕዝብ መሰጠት በዚህ ይታወቃል ። ለእግዚአብሔር ሕዝብ የተሰጡን ምእመናን ለማፍራት የሚችለው ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ ነው ። መድረካችን ለእግዚአብሔር ሕዝብ የተሰጡትን ምእመናን ማፍራት ካልቻለ ራሳችንንም ፥ መድረካችንንም



መመርመር አለብን ። ለምን ማፍራት እንዳቃተን በጾምና በጸሎት መድረካችንን መመዘን ፥ ጌታንም መጠየቅ ። መልስ እናገኛለን።

## ላልዳኑት ነፍሳት ደህንነት መሰጠት

ሶስተኛው የምእመናን መሰጠት ላልዳኑት ነፍሳት ደህንነት መሰጠት ነው ። እኛ የተቀበልነውን የኃጢአት ይቅርታ መቀበል አለባቸው ። እኛ የተቀበልነውን የዘላለም ሕይወት መቀበል አለባቸው ። እኛ ያገኘነውን የአእምሮ ሰላም ፥ የልብ ደስታና የሕይወት እርካታ መቀበል አለባቸው ። ይህ ሊሆን የሚችለው ምእመናን ለነፍሳት ደህንነት የጽድቅ መሣሪያ ሆነው ሲሰጡ ብቻ ነው።

ለእግዚአብሔር መሰጠት ብቻ በቂ አይደለም ። ለምእመናንም መሰጠት አለብን ። ለምእመናን መሰጠት ብቻ በቂ አይደለም ። ለነፍሳት ደህንነትም መሰጠት አለብን ። ይህ ሐላፊ ነታችንም ፥ እድል ፈንታችንም ነው ።

“ ሳውልም በእስጢፋኖስ መገደል ተስማምቶ ነበር ። እስጢፋኖስ በሞተበት ቀን በኢየሩሳሌም በምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ተነሣ ፤ ከሐዋርያት በቀር አማኞች ሁሉ ወደ ይሁዳ አገርና ወደ ሰማርያ አገሮች ተበተኑ ........ የተበተኑትም አማኞች በሄዱበት ስፍራ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ያስተምሩ ነበር ” ( የሐ ዋ 8:1 ፥ 4 ) ።

እነዚህ ምእመናን በእምነታቸው ምክንያት ቤትን ፥ ንግድን ፥ እርሻን ዘመዶችን እርግፍ አድርገው የተሰደዱ ምእመናን እንደነበሩ ዓይተናል ። እነዚህ ለጌታ የተሰጡ አማኞች ስለነበሩ ነው ሊሰደዱ

የቻሉት ። በተበትኑባቸው ከተሞችና መንደሮች ፣ በእምነታቸው ምክንያት ሌላ ስደት እንዳይደርስባቸው በመፍራት ስለ ክርስቶስ አዳኝነት ላለመናገር ይችሉ ነበር ።

ነገር ግን ዝም ለማለት አልቻሉም ። ስለ ክርስቶስ አዳኝነት መናገር ነበረባቸው ። ምክንያቱም የተሰጡ ምእመናን ነብሩ ። መስጠታቸው ደግሞ ለክርስቶስና ለክርስቶስ ተከታዮች ብቻ አልነበረም ። ላልዳኑት ፣ በይሁዳና በሰማርያ ከተሞችና መንደሮች እንዲሁም ገጠሮች ላሉት ነፍሳትም ጭምር ነበር ። የተሰጡ ስለነበሩ ዝም ለማለት አልተቻለም ። “ በሄዱበት ስፍራ ሁሉ ” የክርስቶስን አዳኝነት አወጁ ።

ይህን በማድረጋቸው ዋጋ ሊያስከፍላቸው እንደሚችል አልዘነጉም ። ነገር ግን የተሰጡ ስለ ነበሩ ዋጋውን ለመክፈል ፈቃደኞች ነበሩ ። ስለ ሲኦል አስቃቂነትና ስለ መንግሥተ ሰማይ አስደናቂነት በሚገባ ያውቁ ነበር ። የተሰጠ ምእመን ስለ ሲኦል አስቃቂነትና ስለ መንግሥተ ሰማይ አስደናቂነት እያወቀ የክርስቶስን አዳኝነት ለነፍሳት ከማወጅ ዝም ለማለት አይችልም ።

ያልተሰጠ ሰው ብቻ ነው “ እኔ ወንጌላዊ ወይም እረኛ ወይም የመስካሪ ቡድን አባል አይደለሁም ” በማለት ስለ ክርስቶስ አዳኝነት ለነፍሳት የማወጅን ሐላፊነት ለሌሎች የሚተው ። አዎን ወንጌላዊ ፣ የመስካሪ ቡድን ፣ እረኛ ይህን አስደናቂ አዋጅ ማወጅ አለባቸው ። ይህን ማለት ሌሎች ምእመናን ዝም ይበሉ ማለት አይደለም ። ዝም ማለት አይገባም ። በደል ነው ።

እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የኢየሩሳሌም ምእመናን ይህን ሐላፊነት ለወንጌላዊ ፊሊጶስ አልተውም ። “ በመካከላችን



ፊሊጶስ ስላለ እርሱ ይመስክርላቸው ። ምክንያቱም ይህ የእርሱ ጥሪ ነው ” አላሉም ። እርሱም የራሱንድርሻ ፣ እነርሱም የራሳቸውን ድርሻ ተካፈሉ ( የሐ ዋ 8:4-7 ) ። ውጤቱ ምን ሆነ ? የክርስቶስ አዳኝነትና ፈዋሽነት በድፍረት ታወጀ ። “ ስለዚህ በዚያ ከተማ ታላቅ ደስታ ሆነ ” ( የሐ ዋ 8:8 ) ።

በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ ብቻ ነው እንደ ኢየሩሳሌም ምእመናን የተሰጡትን አማኞች ለማፍራት የሚችለው ። የነፍሳትን ደህንነት ቸል የሚል ጉባኤ የጥያቄ ምልክት አለበት ። ለነፍሳት ደህንነት ራሳቸውን ያልሰጡ ምእመናን ካሉን መድረካችንን መመርመር አለብን ። በተዋረደ መንፈስ ፣ በጾምና በጸሎት እግዚአብሔርን እንጠይቅ ። ያሳየናል ። ይጠቁመናል ።

ሁሉም ወንጌላዊ አይደለም ። ሁሉም እረኛ አይደለም ። ሁሉም የመስካሪ ቡድን አባል አይደለም ። ነገር ግን ሁሉም “ አማኞች በሄዱበት ስፍራ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ” ላልዳኑት ነፍሳት መናገር አለባቸው ( የሐ ዋ 8:4 ) ። ይህ የመስጠት ምልክት ነው ።

ስለዚህ መድረካችን በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ ከሆነ የምናፈራቸው ምእመናን አንደኛ ለእግዚአብሔር የተሰጡ ምእመናን ይሆናሉ ። ሁለተኛ ለእግዚአብሔር ሕዝብ የተሰጡ ምእመናን ይሆናሉ ። ሶስተኛ ለነፍሳት ደህንነት የተሰጡ ምእመናን ይሆናሉ ። እነዚህ ሶስት ዓይነት መሰጠቶች የሚነጣጠሉ አይደሉም ። ከሶስቱ አንዱም መጉደል የለበትም ።

## ሰዎችን ከልዩ ልዩ እስራቶች ናፃ ያወጣል

በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ ሰዎችን ከጨለማ ወደ እግዚአብሔር ብርሃን መመለስ ብቻ ሳይሆን ወደ እግዚአብሔር የተመለሱትንም ከልዩ ልዩ እስራቶች ነፃ ያወጣል ። ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ሲመለሱ ስላለፈው ኃጢአታቸው ወዲያውኑ ምህረትን ያገኛሉ ። ወዲያውኑ ቢሞቱ የእግዚአብሔርን መንግሥት ይወርሳሉ።

ነገር ግን ወደ ጌታ ከመመለሳቸው በፊት ከተጣበቁባቸው ልዩ ልዩ እስራቶች ነፃ ወጥተዋል ማለት አይደለም ። ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን ለመቀበል እጁን ሲያነሣ ቅጽበታዊ በሆነ ሁኔታ በሕይወቱ ከነበሩት ልዩ ልዩ እስራቶች ናፃ እንደ ወጣ መገመት ስህተት ይሆናል ። ከእነዚህ ትብታቦችና እስራቶች ለመላቀቅ ጊዜ ይጠይቃል ። ይሁን እንጂ መድረኩ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ ከሆነ ሰዎችን ከማናቸውም ልዩ ልዩ እስራቶች ነፃ እንደሚያወጣ የታወቀ ነው ።

### 1ኛ/ ከልዩ ልዩ መጥፎ ልማዶች ነፃ ያወጣል

“ ዓመጸኞች የእግዚአብሔርን መንግስት እንደማይወርሱ ታውቁ የለምን ?በዚህ ነገር አትታለሉ ፡ ሴሰኞች ወይም ጣኦት አምላኪዎች ወይም አምንዝራዎች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚያደርጉ ወንዶች ፡ ወይም ሌቦች ወይም ስግብግቦች ወይም ሰካራሞች ወይም የሰው ስም አጥፊዎች ወይም ቀማኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም ። ከእናንተም አንዳንዶቻችሁ እንዲሁ ነበራችሁ ፤ አሁን ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና በአምላካችን መንፈስ ከኃጢአት ታጥባችኋል ፡ ለእግዚአብሔር የተለየ ቅዱስ



ሕዝብ ሆናችኋል ፤ ጸድቃችኋልም ” ( 1ቆሮ 6:9:11 ) ።

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ጥቅሶች ውስጥ ዘጠኝ የሚሆኑ ልዩ ልዩ የጽድቅ ተቃራኒዎች ተጠቅሰዋል ። እነዚህም :-ሴሰኝነት ፡ ጣኦት አምላኪነት ፡ አመንዝራነት ፡ ሰዶማዊነት ፡ ሌብነት ፡ ስግብግብነት ፡ ሰካራምነት ፡ ስም አጥፊነት ፡ ቀማኛነት ናቸው ።

በቆሮንቶስ ምእመናን መካከል አንዳንዶቹ ወደ ክርስቶስ ከመመለሳቸው በፊት በእነዚህ መጥፎ ልማዶች የተተበተቡ ነበሩ ። ሕይወታቸውና እለታዊ ኑሮአቸው በእነዚህ ርኩሰቶች የተጨማለቀ ነበር ። እነዚህ ርኩሰቶች እለታዊ ልምምዶቻቸው ነበሩ ።

ነገር ግን ሐዋርያው ጳውሎስ በቆሮንቶስ ከተማ በመሠረተው መድረክ እነዚህ ሰዎች ከጨለማ ወደሚደነቀው የእግዚአብሔር ብርሃን ተመለሱ ። ከዚያ በፊት ሕይወታቸውን አስረው ከነበሩት ልዩ ልዩ ርኩሰቶችም ነፃ ወጡ ። የሕይወታቸውም ታሪክ በማያዳግም ሁኔታ ተለወጠ ።

ሐዋርያ ጳውሎስ የቀድሞ ሕይወታቸውንና የአሁኑን እያነጻጸረ ሲገልጥ እንዲህ ይላል ፡ “ ከእናንተም አንዳንዶቻችሁ እንዲሁ ነበራችሁ ፤ አሁን ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና በአምላካችን መንፈስ ከኃጢአታችሁ ታጥባችኋል ፤ ለእግዚአብሔር የተለየ ቅዱስ ሕዝብ ሆናችኋል ፤ ጸድቃችኋልም ” ( 1ቆሮ 6:11 )።

አዎን በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ ከጣኦት እስራት ነፃ ያወጣል ። ከዝሙት እስራት ነፃ ያወጣል ። ከመጠጥ እስራት ነፃ ያወጣል ። ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠራውን ወንድና ከሴት

ጋር ዝሙት የምትሠራዋን ሴት ከዚህ ከሰዶማዊነት እስራት ነፃ ያወጣል ። የአዋቂ ምክርና የራስ ቆራጥነት ብቻ ከእነዚህ ርኩሰቶች ነፃ ሊያወጣ አይችሉም ። በመንፈስ ቅዱስ ከተሞላ መድረክ የሚታወጀው የወንጌል ኃይልና የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ነው ነፃ ሊያወጣ የሚችል ።

በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ ከሚታወቅባችውና ከሚመዘንባቸው ነገሮች መካከል አንዱ የሰዎች ከልዩ ልዩ ርኩሰቶች ነፃ መውጣት ነው ። በመድረካችን አገልግሎት ሰዎች ከልዩ ልዩ ርኩሰቶች ወይም ልማዶች ናፃ የማይወጡ ከሆነ መድረካችንን መመርመር አለብን ። በጾምና በጸሎት ጌታን መጠየቅ አለብን።

የቆሮንቶስ ሰዎች ከእነዚህ ከባድና ተጠባቂ ርኩሰቶች ነፃ ለመውጣት ከቻሉ በዘመናችን ያሉት ሰዎችም ከርኩሰቶቻቸውና ከክፉ ልማዶቻቸው ነፃ መውጣት ይችላሉ ። የእግዚእብሔር ኃይል የሰውን ታሪክ ይለውጣል ። በዘመናችንም ቢሆን እግዚአብሔር የመለወጥን ሥራ ሲሠራ ዓይተናል ። የመድረካችንም ፍሬ በዚህ ሊመዘንና ሊታወቅ ይገባል ።

## 2ኛ/ ከተሳሳተ አመለካከት ሰውን ነፃ ያወጣል

ትምህርትና ምክር የሰውን አመለካከት ለማሻሻል ይችላሉ ። ነግር ግን ለመለወጥ የሚችለው የእግዚአብሔር ኃይል ብቻ ነው ። በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ የሰውንም አመለካከት በሚያስገርም ሁኔታ ይለውጣል ።

ለምሳሌ የዘረኝነትን አመለካከት ፥ “ እኛ ” ፥ “ እነርሱ



” የሚለውን አምለካከት ፥ “ ሃብታም ” ስለ “ ድሃ ” ያለውን አመለካከት ለመለወጥ የሚችለው በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ ብቻ ነው ። ይህን አመለካከት ማሻሻል ሳይሆን ሥሩን ነቅሎ ለመጣልና በዚህ ፈንታ ሰማያዊ አመለካከትን በምእመናን ሕይወት ውስጥ የሚመሠርተው በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ ብቻ ነው ።

የኢየሩሳሌም ከተማ ሕዝብ “ እኛ ” ፥ “ እናንተ ” “ እነርሱ ” በሚል አምለካከት ይተያዩና ይተሳሰቡ ነበር ( ዮሐ 4:5-30 ) ። የኢየሩሳሌም ከተማ ሰዎች የሰማርያን ከተማ ሰዎች ይጠሉ ፥ ይንቁና ይጸየፉ ነበር ። የኢየሩሳሌም ሰዎች ለሰማርያ ሰዎች የነበራቸውን አምለካከት ከዚህ ቀጥሎ ባለው ጥቅስ ውስጥ ለመመልከት እንችላለን ፤ “ አይሁዳውያንም አንተ ሳምራዊ ነህ ፤ ጋኔንም አለብህ ፤ ማለታችን ልክ አይደለምን ? አሉት ” ( ዮሐ 8:48 ) ።

ይህን የተናገሩት ኢየሱስን ለመስደብ ነበር ። ነገር ግን ሰማርያውያንን ተጠቅመው ነበር የሰደቡት ። ይህን የመሰለ አመለካከት ስለነበራቸው ነው የሰማርያውያንን ውሃ የማይጠጡት ፥ እህላቸውን የማይበሉት ፥ በከተማቸውና በመንደራቸው የማያልፉት ።

ነገር ግን እንደዚህ ዓይነቱን ቆሻሻ አመልካከት የነበራቸው የኢየሩሳሌም ከተማ ሰዎች አስገራሚና አስደሳች ነገር ሲሠሩ እናያቸዋለን ። በኢየሩሳሌም ከተማ ታላቅ ስደት በተነሣ ጊዜ ምእመናን የሄዱት ወደ ሰማርያ ከተሞችና ሕዝብ ነበር ( የሐ ሥ 8:1) ። መሄድ ብቻ ሳይሆን ከኃጢአት ፥ ከልዩ ልዩ እስራቶች ፥ ከዘረኝነትና ከመጥፎ አመልካከት ናፃ የሚያወጣውን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ሰበኩላቸው ።

ይጸየፉት የነበረውን የሰማርያውያን ውሃ ጠጡ ፤ ምግባቸዉን በሉ ። በመካከላቸው ሰፈሩ ። በኢየሩሳሌም ከተማ ሆኖ እንዳነበረ " በዚያች ከተማ ታላቅ ደስታ ሆነ " ( የሐ ሥ 8:8 ) ። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ ? በመንፈስ ቅዱስ ከተሞላበት መድረክ የታወጀው የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ስለ ለወጣቸው ነው ።

አመለካከታቸው አልተሻሻለም ። ነገር ግን ሥር ነቀል የሆነ ለውጥ በሕይወታቸው ተሠራ ። መድረካችን በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ ሲሆን ብቻ ነው " እኛ ፥ " እነርሱ " ፥ " እናንተ " የሚለው አምለካከት የሚለወጠው " መድረካችን በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሲሆን ብቻ ነው ከምእመናን ሕይወት የዘረኝነትን አመለካከት ነቅለን ለመጣል የምንችለው ። መድረካችን በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ከሆነ ሥር ነቀል የሆነ ለውጥ በምእመናን ሕይወት ውስጥ ያመጣል ።

እልልታና ጭብጨባ ሥር ነቀል የሆነ ለውጥ አያስገኝም ። እልልታና ጭብጨባ ክልዩ ልዩ እስራት ነፃ አያደርግም ። በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ ብቻ ነው ዘለቄታ ያለው ፥ በተግባርና በእለታዊ ኑሮ ሊታይ የሚችለውን ለውጥ የሚያስገኘው።

መድረካችን ሞቅ ሞቅ ለማድረግ ብቻ ከሆነ የመድረክ ሥራ ምን እንደሆነ ገና አልገባንም ማለት ነው ። መድረካችን በምእመናን ሕይወት ውስጥ ሥር ነቀል ለውጥ የማያመጣ ከሆነ በእውነትና በትህትና ፥ በጾምና በጸሎት መመርመርና መመዘን አለበት ። ምክንያቱም በመንፈስ ቅዱስ የትሞላ መድረክ የምእመናንን ሕይወት ይለውጣል ።



## 3ኛ/ ከሕመም ነፃ ያወጣል

አንዳንድ የሕክምና አዋቂዎች ባደርጉት ጥናት መሠረት ሰዎችን ወደ ሐኪም ቤት የሚያስሄዱዋቸው ሕመሞች ከመቶ ሰማኒያው እጅ (80 %) በሥጋ ሕመሞች ላይ የተመሠረቱ እንዳልሆኑ ይናገራሉ ። ይህም ማለት በራጅ የማይታይና ተቀዶ የማይጠገን ሕመም ማለት ነው ።

እርግጥ ነው ይህ ጥናት ዓለም አቀፍ ጥናት ስላልሆነ የአንዱ ሕብረተሰብ ሁኔታ ከሌላው ሕብረተሰብ ሁኔታ ሊለይ ይችላል ። ይሁን እንጂ ጥናቱ እውነትነት ያለው ጥናት መሆኑ አይካድም ።

በሥጋ ሕመም ላይ ያልተመሠረቱና ጤናን የሚያቃውሱ ብዙ ነገሮች እንዳሉ የታወቀ ነው ። ለዚህ የሕክምና ጥናት እንኳ አያስፈልግም ። ሁላችንም በእለታዊ ኑሮአችን የምንለማመዳቸው ብዙ የጤና ጠንቆች አሉ ።

በተለይም በእግዚአብሔር ቃል ውስጥየተጻፉና እኛ ግን ለጤናችን ጠንቆች መሆናቸዉን ያልተገነዘብናቸው ብዙ ነገሮች አሉ ። እነዚህን ለመንፈሳዊም ሕይወት ሆነ ለጤናም ሕይወት ጠንቆች የሆኑትን ነገሮች ከዚህ ቀጥዬ እጠቅሳቸዋለሁ ።

ልማዳዊ መጨነቅ ፥ ልማዳዊ ቁጣ ፥ መራራነት ፥ ልማዳዊ ንዴት ፥ይቅር ያለ ማለት ፥ ልማዳዊ ፍርሃት ፥ " ዋጋ የለኝም " ወይም " ለምንም ነገር አልጠቅምም " የሚል ስሜት ፥ " ማንም አይፈልገኝም " ወይም " ማንም ሰው አይወደኝም

የሚል ስሜት ፥ ምቀኝነት ፥ ቅንአት ወዘተ ።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ነገሮች ለመንፈሳዊ ሕይወት ምን ያህል ጠንቆች እንደሆኑ በምእመናን ዘንድ የታወቀ ስለሆነ ብዙ መዘርዘር አስፈላጊ አይመስለኝም ። ለግል መንፈሳዊ ሕይወት ፥ ለአገልግሎት ሕይወት ፥ ለትዳር ሕይወት ወዘተ ጠላቶች ናቸው ። እነዚህን በሕይወት ይዞ መኖር በኃጢአት መኖር እንደሆነ ግልጽ ነው ።

ከመንፈሳዊ ሕይወትም አልፎ ለጤናችን መቃወስ ብዙ ጊዜ ምክንያት የሚሆኑት እነዚህ ጠንቆች ናቸው ። ለዚህ ነው ብዙዎች ሐኪም ቤት ሲሄዱ ሐኪም በሽታቸውን ማወቅ ወይም ማግኘት የሚያቅተው ። እነዚህ ነገሮች የሚፈጥሩዋቸው ሕመሞች በሐኪም ራጅ የሚታዩ አይደሉም ። ለዚህ ነው ሰዎች “ ሐኪም ቤትም ሄጃለሁ ፤ ራጅም ተነስቻለሁ ፥ ነገር ግን በሽታዬን ሐኪሞች እንኳ ሊያውቁልኝ አልቻሉም “ የሚሉት ።

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ጠንቀኞች ነገሮች ምክንያት የሚመጡትን ሕመሞች ከሕይወታችን ሊደመስስ  የሚችለው የእግዚአብሔር ኃይል በቻ ነው ።

በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መድረክ ከአጋንንት ነፃ ያወጣል ። በራጅ ከሚታዩም ከማይታዩም ልዩ ልዩ ሕመሞች ነፃ ያወጣል ። በመንፈስ ቅዱስ ከተሞላ መድረክ ያለ ማቋረጥ የሚተላለፈው የቃሉና የመንፈሱ ኃይል ቀንበርን ይሰብራል ፤ ከእስራት ይፈታል ፤ እርነትን ይሰጣል ፤ የውስጡንም ሆነ የውጭውንም ፈውስ ያስገኛል ።



እዚህ ላይ አንድ ማሳሰቢያ ሳልሰጥ ይህን ምዕራፍ ለመደምደም አልፈልግም ። አንዳንድ ጊዜ ከመድረኩም ፥ ከሕመምተኞችም ፥ ከሚጸልዩም ሰዎች ምንም ጉድለት ሳይኖር የተጸለየላቸው ሕመምተኞች የሥጋ ፈውሳቸውን የማይቀበሉበት ጊዜ አለ ። ምክንያቱ የእምነት ማጣት አይደለም ፤ የተሰወረ ኃጢአትም ኖሮ አይደለም ። ምክንያቱ አይታወቅም ።

እንደዚህ በሚሆንበት ጊዜ ርካሽ መልስ ከመስጠት መቆጠብ አስተዋይነት ነው ። ርካሽና በእግዚአብሔር ቃል የማይደገፍ መልስ ለመስጠት ብንሞክር ሕመምተኛውን የባሰውኑ ሕመምተኛ እናደርገዋለን ። በእግዚአብሔር ላይ ያለውንም እምነቱን ልናናጋበት እንችላለን ። በእምነትና በቅድስና ከእኔ የማያንሱ ምእመናን አውቃለሁ ። ነገር ግን እኔ ተፈውሻለሁ ፤ እነርሱ ግን አልተፈወሱም።

ለሕመምተኞች ፈውስ እንዲጸልዩ እግዚአብሔር የፈውስ ስጦታ ከሰጣቸው አገልጋዮች መካከል አንዳንዶቹ የራሳቸው የጤና ችግር ያለባቸው አገልጋዮች እንዳሉ የታወቀ ነው ። እነዚህን ሰዎች ለማወቅ በአእምሮ አትንከራተቱ ።

ኢትዮጵያዊ ያልሆነ አንድ አገልጋይ አውቃለሁ ። ይህ አገልጋይ ከሃያ አምስት ዓመታት በላይ ለሕመምተኞች ሲጸልይ የኖረ አገልጋይ ነበር ። ለሕመምተኞች ሲጸልይ ብዙዎች ይፈወሱ ነበር ። እኔ ራሴ ዓይቻለሁ ። ከዚህ ሰው ጋር በነጮች መካከል ደጋግሜ አገልግያለሁ ።

ነገር ግን ራሱ ትልቅ ሕመም ነበረበት ። የእርሱ ዓይነት ሕመም ላለባቸው ሕመምተኞች ጸልዮላቸው ብዙዎች ተፈውሰዋል ። ይህን ሰው ሁሉ ያውቃል ። የእርሱ ጤናና እግዚአብሔር

በእርሱ አማካይነት ለሌሎች ሕመምተኞች የሚሠራው ሥራ ስለተጋጨብኝ በግልጽ ጠየቅሁት ። እርሱም በግልጽ ነገረኝ ። ለብዙ ዓመታት በጸምና በጸሎት ፥ በብዙ እንባ እግዚአብሔርን ሲጠይቅ እንደ ኖረና ከእግዚአብሔር ምንም ፈውስ መቀበል እንዳልቻለ አጫወተኝ ።

አንድ ቀን እንደተለመደው በጸምና በጸሎት ፥ በብዙ እንባ ስለ ጤናው በእግዚአብሔር ፊት ቀረበ ። " ከዛሬ ጀምሮ ስለ ጤናህ ጉዳይ በፊቴ እንዳትቀርብ ። ነገር ግን እንደ ጠራሁህ አገልግሎትህን ቀጥል " በማለት እግዚአባሔር እንደ ተናገረው ነገረኝ ።

ከዚያም በኋላ በዚያው ሁኔታ ሌሎችን ሕመምተኞች ሲያገለግል ከኖረ በኋላ በቅርብ ጊዜ ወደ ጌታው እንደሄደ አውቃለሁ ። ቁጭ ብለን በግልጽ ከተጫወትነው ጫወታችን እንደተረዳሁት ፥ የተሰወረ ኃጢአትም አልነበረም ፤ የእምነትም ጉድለት አልነበረም ። ጉዳዩን እርሱም እኔም አናውቅም ። እግዚአብሔር ብቻ ነው የሚያውቀው ።

ነቢዩ ኤልሳዕ በአገልግሎት ዘመኑ ብዙ ተአምራትን ያደረገ አገልጋይ ነበር ። የሞተውንም ሰው ከሞት አስነስቷል ( 2ነገሥ 4:35 ) ። እርሱ ራሱ ግን የሞተው " በብርቱ ደዌ ታሞ " ነው ። በዚህ ደዌ በመሞት ላይ እያለ የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ መጣ ። ትንቢትንም ተናገረ ፤ ለንጉሡም መመሪያን ሰጠ ። የእግዚአብሔርን መልእክት ለንጉሡ አስተላልፎ ሲያበቃ በዚያው " በብርቱ ደዌ " ሞተ ( 2ነገሥ 13:14-20 ) ። የተሰወረ ኃጢአት ነው ? የእምነት ጉድለት ነውን ? አይደለም ። ምሥጢሩ ለእግዚአብሔር ነው።



እግዚአብሔር ይፈውሳል ። እኔ ራሴ ምስክር ነኝ ። ደጋግሞ ደጋግሞ ፈውሶኛል ። ሌሎችንም ሲፈውስ አይቻለሁ ። ቃሉም ይናገራል ። ይሁን እንጂ ጉድለት ከመድረኩም ሳይኖር ፥ ከሚጸልየውም ሰው ሳይኖር ፥ ከሕመምተኛውም ሳይኖር ሕመምተኛው የሥጋ ፈውሱን የማይቀበልበት ጊዜ አለ ። ምክንያቱ ምን ይሆን ? አናውቅም ። አላውቅም ። የማላውቀውን ነገር አላውቅም ማለትን ተምሬአለሁ ። " ምሥጢሩ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው " ( ዘዳ 29:29 ) ።

ታድያ ስለ ፈውስ ማወጁን እናቁም ? ለሕመምተኞች መጸለዩን እንተው ? ከቶ አይሁን ! የእግዚአብሔርን ፈዋሽነት እናውጃለን ። ለሕመምተኞችም እንጸልያለን ። ምሥጢሩንም ለአምላካችን ለእግዚአብሔር እንተዋለን ። ርካሽ መልስና ርካሽ ምክር ግን አንስጥ ። እንጠየቅበታለንና ።

ETHIO...
DALLAS, TX 75218

# መደምደሚያ

የተልእኮ አሳብ በእግዚአብሔር አእምሮ ያልነበረበት ጊዜ የለም ። የእሥራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔር መልእክተኛ በመሆን የዓለምን ሕዝቦች ወደ እግዚአብሔር እንዲመልሱ ነበር የተጠሩት።

ይሁን እንጂ የእሥራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔርን የተልእኮ ምስጢር ስላልተገነዘቡና ስላልፈጸሙ የእግዚአብሔር እቅድ እንደታሰበ ከግቡ ሳይደርስ ቀረ ።

ነገር ግን እግዚአብሔር እቅዱን ሳይፈጽም የማይቀር አምላክ ስለሆነ ጊዜዉን ጠብቆ ( ገላ 4:4 ) በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት የተልእኮዉን እቅድ በግልጥና አስገራሚ በሆነ ሁኔታ ገለጠ ።

ከዚህ የተነሳ ይህ አስደናቂ ተልእኮ ከእግዚአብሔር አብ ወደ ልጁ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ተላለፈ ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለዚህ ተልእኮ ሲናገር እንዲህ አለ ።



" የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው ፤ መልካም ዜናን ለድሆች እንዳበስር ሾሞኛል ፤ ለታሠሩትም መፈታትን ፥ ለታወሩትም ማየትን እንዳውጅና የተጨነቁትን ነፃ እንዳወጣ ልኮኛል " ( ሉቃ 4:18 ) ።

እግዚአብሔር አብ ይህን ተልእኮ ለልጁ ለኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስተላለፈው ፥ ኢየሱስ ክርስቶስም ይህን ተልእኮ ለተከታዮቹ ወይም ለቤተ ክርስቲያን እንዲህ ሲል አስተላለፈ ፤ " አብ እኔን እንደላከኝ እኔም እናንተን እልካችኋለሁ " (ዮሐ 20:21 ) ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተጨማሪ እንዲህ ሲል ቤተ ክርስቲያንን አዘዘ ፤ " ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ፤ ያዘዝሁአችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ " ( ማቴ 28:18-2 ) ።

ይህ ነው የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ። የእግዚአብሔር አብ የልቡ ትርታ የነበረው ተልእኮ የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ የልቡ ትርታ ሆነ ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ሲገልጥ እንዲህ አለ ፤ " የእኔ ምግብ የላከኝን ፈቃድ ማድረግና ሥራውንም መፈጸም ነው ። እናንተ ገና አራት ወር ቀርቶታል ፤ ከዚያም በኋላ መከር ይሆናል ትሉ የለምን ? እኔ ግን ቀና በሉና እርሻዎቹን ለመከር እንደደረሱ ተመልከቱ እላችኋለሁ "( ዮሐ 4:34-35 )።

የዚህን ተልእኮ ታላቅነት በሚገባ የተረዳው ሐዋርያው

ጳውሎስ ከዚህ እንደሚከተለው የውስጡን ስሜቱን ይገልጣል ፤ “ እኔ ግን አገልግሎቴን እስከፈጽምና ጌታ ኢየሱስ የሰጠኝን ሥራ እስካከናውን ድረስ ለገዛ ሕይወቴ እንኳ አልሳሳም ፤ አገልግሎቴም የእግዚአብሔርን የጸጋ ወንጌል ማብሠር ነው ” ( የሐ ሥራ 20፡24 ) ።

የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልቡ ትርታ እንደሆነ ሁሉ የእኛም የቤተ ክርስቲያኑ የልብ ትርታ መሆን አለበት ። ከእኛ በፊት የነበሩት ምዕመናን ለዚህ ተልእኮ እንደኖሩና እንደ ሞቱ ሁሉ እኛም በዚህ ዘመን የምንኖር የክርስቶስ ተከታዮች ለዚህ ቅዱስና ታላቅ ተልእኮ መኖርና መሞት አለብን ።

# አሜን

ETHIOPIAN EVANGELICAL CHURCH
GARLAND RD.
DALLAS, TX 75218